# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በግብርና ሚኒስቴር የአበባ እርሻ ልማት

## ምርታማነት እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን ለመገምገም የተካሄደ የአካባቢ ኦዲት ሪፖርት



**ጥር 2015 ዓ/ም**

## ማውጫ


**የአካባቢ ኦዲቱ ማጠቃለያ** ........ V

ክፍል አንድ ........ 10

መግቢያ ........ 10

የግብርና ሚኒስቴር ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ስልጣንና ተግባር ........ 11

ራዕይ ........ 11

ተልዕኮ ........ 11

የግብርና ሚኒስቴር ስልጣንና ተግባር ........ 11

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀትና የሰው ኃይል ........ 12

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት ........ 12

የሰው ኃይል ........ 13

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 13

መደበኛ በጀት አፈፃፀም ........ 13

ካፒታል በጀት አፈፃፀም ........ 14

የኦዲቱ ዓላማ ........ 14

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ ........ 14

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 14

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........ 15

የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ........ 15

የኦዲቱ ወሰን ........ 15

የኦዲቱ ዘዴ ........ 16

የሆርቲካልቸር ልማት መሪ ስራ አስፈፃሚ ስራ ሂደት የስራ ፍሰት ........ 17

ኢንቨስትመንት እና ምርት ግብይት መሪ ሥራ አስፈፃሚ የስራ ፍሰት፡ ........ 18

ክፍል ሁለት ........ 19

የኦዲት ግኝቶች ........ 19

ፖሊሲ፣ስትራቴጂ፣ ፍኖተ ካርታ እና ስታንዳርድ ማዘጋጀታቸውን በተመለከተ፡- ........ 19

የአበባ እርሻ ምርቶች እንዳይበላሹ የኮንሶሊዳሽን የህግ ማዕቀፍ መዘጋጀቱን በተመለከተ ፡ ........ 20

የአበባ አልሚ ድርጅቶች የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች የሚያደርሱት ተፅጽኖ ላይ ጥናት መደረጉን በተመለከተ፡ ........ 21

የአበባ እርሻ ልማት የሚጠቀሙት ኬሚካሎች አያያዝ እና የአወጋገድ መመሪያ መዘጋጀቱን በተመለከተ፤ ........ 24

የአበባ እርሻ የሚጠቀሚቸዉን ግብዓቶች እና ተረፈ ምርቶች ምርመራ የሚደረግበት የላብራቶሪ ማዕከል ስለመዘርጋቱ በተመለከተ፤ ...... 28
በአበባ ልማት ዘርፍ የሚከሰቱት ማነቆዎችን ለመፍታት ጥናት መካሄዱን በተመለከተ፤ ...... 30
የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤ ...... 32
በአከባቢ ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት መመሪያዎችን እና ማኑዋሎችን መዘጋጀቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ ...... 33
የአበባ እርሻ ድርጅቶች የአከባቢ ኦዲት ማስደረጋቸውን በተመለከተ፤ ...... 35
የአፈር ምርመራ በማድረግ የማከም ስራ መስራታቸውን መከታተሉን በተመለከተ፤ ...... 37
የመሬት ልየታ በማድረግ እንዲሰጥ ማድረጉን በተመለከተ፤ ...... 39
የአበባ እርሻ ልማቱ የሚጠቀሙትን ግብዓት መጠንና አይነት፣ አጠቃቀምና የክትትል ስርዓትን በተመለከተ፤ ...... 41
የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ በተመለከተ፤ ...... 43
የመልካም እርሻ አተገባበር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን በተለመከተ፤ ...... 44
የፀረ-ተባይ ኬሚካል ግብዓቶች ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱን ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ ...... 45
የአበባ አልሚ ድርጅቶች የማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ እና የአከባቢ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀታቸውን በተመለከተ ...... 47
የአበባ አልሚ ድርጅቶች የተቀናጀ ተባይ መከላከል /IPM/ እንዲተገበሩ ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ ...... 49
በአበባ ልማት ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች የሰብአዊ መብቶች፣ የስራ አከባቢ የደህንነትን በተመለከተ፡ ...... 50
በአበባ አልሚ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ሴት ሠራተኞች ጤንነታቸውና እና የስራ ቦታ ደህንነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸው መጠበቁን በተመለከተ፡ ...... 54
የቆሻሻ አያያዝና እና አወጋገድ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡ ...... 56
የማህበራዊና የአከባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎችን አሟልተው እየሰሩ ስለመሆናቸው ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፡ ...... 59
ለአልሚዎች የተላለፈው መሬት አጠቃቀም በተመለከተ ...... 61
የአበባ እርሻ ልማት ግብይት ወቅታዊ፣ የምርትና የግብይት መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረጉን በተመለከተ ...... 63
ከሀገር ውስጥና ከውጪ ተሞክሮዎችን በመቀመር ቋሚ የምክክር መድረክ ማዘጋጀቱን በተመለከተ ...... 65
ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋቱን በተመለከተ ...... 66
ክፍል ሶስት ...... 67

*መደምደሚያ* ........ 67

ክፍል አራት ........ 72

*የማሻሻያ ሃሣቦች* ........ 72

አባሪ-1 ........ 77

የግብርና ሚንስቴር ስልጣንና ተግባር ........ 77

የግብርና ሚንስቴር መዋቅር

አባሪ 2 ........ LXXXI

መመዘኛ መስፈርት አባሪ 3 ........ LXXXII

**አባሪ 4** ........ LXXXVII

**ለአበባ እርሻ የተሰጣቸው መሬት ያላለሙ ድርጅቶች** ........ LXXXVII

## የአካባቢ ኦዲቱ ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ የተፈጠረውን ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታን በመከተል እንደማንኛውም የኢንቨስትመንት ዘርፍ ካለፉት 15 ዓመታት ወዲህ በግብርና ዘርፍ ውስጥ በሚካተተው የሆርቲካልቸር ንዑስ ዘርፍ ኢንቨስትመንት ላይ የአገር ውስጥ እና የውጪ ባለሀብቶች በስፋት በመሳተፍ ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ የሆርቲካልቸር ንዑስ ዘርፍ በዋነኛነት የሚካተቱት የምርት አይነቶች (አበባና ፣የአበባ ችግኝ፣ ፍራፍሬ፣ አትክልት እና ኸርብስ) ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ አትክልት ፍራፍሬንና አበባን በማልማት ለገበያ የማቅረብ ተግባር በ1974 ዓ.ም. አከባቢ የተጀመረ ስለመሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በተለይም ከዕዝ ኢኮኖሚ ወደ ገበያ መር ኢኮኖሚ ሽግግር ከተደረገ በኋላ የግል እርሻዎች በእጅጉ ተስፋፍተዋል፡፡ ባሁኑ ጊዜ ሀገሪቱ በዚህ መጠነ ብዙ መዋዕለንዋይ በሚጠይቅ ዘርፍ በተለይ በአበባ ኤክስፖርት 60 እርሻዎችን በማንቀሳቀስ እጅግ ከፍተኛ ውጤት እያስመዘገበች ሲሆን፣ ከኬንያ በመቀጠል ከአፍሪካ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ብትገኝም፣ የአበባ እርሻ ልማቱ በባህሪው የሚጠቀሚቸ ግብአቶች ማደበሪያ፣የተለያዩ ፀረ-አረም እና ጸረ-ተባይ ኬሚካሎች በመሆኑ በከፍተኛ ጥንቃቄ ካልተመራ በአካባቢ ስነምሕዳር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡ በመሆኑም መ/ቤታችን የአበባ እርሻ ልማት ምርታማነትና በአከባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነት በሚል ርዕስ በግብርና ሚኒስቴር የአካባ ኦዲት አከናውኗል፡፡

የአካባቢ ኦዲቱ አላማ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ምርታማነትና በአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ አፈጻጸሙ እንዲሻሻል እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

ለአካባቢ ኦዲቱ የተመረጡ የትኩረት አቅጣጫዎች ሦስት ሲሆን እነሱም፡- የአበባ እርሻ ልማት ሂደት ውስጥ ምርታማነቱ እና የምርት ግብዓት አያያዝ ስርዓቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ለመተግበር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱና ተግባራዊነቱን መገምገም፣ የአበባ እርሻ ልማት በሚመረትበት ወቅት በአካባቢው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር የክትትል ሥርዓት መኖሩንና ተግባራዊ ማድረጉን

መገምገም እና ከአበባ  እርሻ ልማት ጋር ተያይዞ የሚመጡትን ማነቆዎች ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን መገምገም ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኦዲቱ የሚያስፈልጉ ማስረጃ በመከለስ፣ የሚመለከታቸውን የስራ ኃላፊዎች በመጠየቅ፣ ባለድርሻ አካላትና የአበባ እርሻ ድርጅቶችን በናሙና በመምረጥ መጠይቅ በማድረግ እና በመስክ ምልከታ፣ እንዲሁም በአበባ እርሻ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችና የአካባቢ ነዋሪዎችን በመጠየቅ ማስረጃዎች በማሰባሰብና በመተንተን ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards of Supreme Audit Institutions (ISSAI) እና በመንግስት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 (በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1146/2011) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ሲሆን፣ በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የአበባ እርሻ በአከባቢው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ እና የዘርፉ ግብይት የሚመራበት የራሱ የሆነ የህግ ማዕቀፎች(ፖሊሲ፣ አዋጆች፣ደንብና መመሪያዎች) እንዲሁም የኮንሶሊዴሽን(consolidation) የህግ ማዕቀፎች፣ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ የህግ ማዕቀፍ፣ የአከባቢ ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት መመሪያም፣ማኑዋል ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣ እንዲሁም የተቀናጀ የተባይ መከላከያ/IPM/ ለመተግበር የህግ ማዕቀፍ አለመዘጋጀቱ፡
- የአበባ እርሻ ልማት ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚጠቀሟቸው  ግብአቶች  ማለትም ኬሚካል፣ ፍሳሽ ቆሻሻ፣ ተረፈ-ምርት፣ የኬሚካል መያዣ ፕላስቲኮች እና ፍሳሽ ቆሻሻ፣ የመሳሰሉት ያለምንም ቅድመ ማጣራት ወደ አከባቢው ማህበረሰብ የሚለቀቁ መሆናቸው፣እንዲሁም የሚጠቀሙት ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም ኬሚካሎች ወደመሬት ሰርጎ በመግባት መሬቱን እንዳይመርዝ የፕላስቲክ ንጣፍ የማይጠቀሙ በመሆናቸው በአፈሩ እና አካባቢው ላይ ጉዳት እያደረሰ መሆኑ፣

- የአበባ እርሻ ልማት የሚጠቀሙት ኬሚካሎች በተገቢው መንገድ ማጓጓዛቸውና በተገቢው መጋዘን ማከማቸታቸውን ለአብነት ቤቲ ኦርናሜንታል፡አሮው ኤክስፖርት፡ሳታያሳይ plc፡ ኦምኒ ብሎሰም፡አቢሲኒያ ፍላወር፡ክላቨር ፍላወር የኬሚካል መጋዘኑ በጣም ጠባብና በቂ የአየር ዝውውር የሌለው መሆኑ፣የኬሚካል አቀማመጡ ጊዜ ያለፈባቸውና ካላለፈባቸው ኬሚካሎች ጋር በአንድ ላይ ተቀላቅለው የሚቀመጡና ማከማቻ መጋዘኑ 50 ሜትር ከፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ የራቀ ሆኖ መገንባት ያለበት ቢሆንም፤ ከጉድጓድ አጠገብ መሆኑ እንዲሁም ኬሚካሉ ሲጓጓዝ ተገቢና ምቹ ባልሆኑ መኪኖች የሚጓጓዝ መሆኑ፣
- የአበባ እርሻ ድርጅቶች የሚጠቀሙት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችና ግብዓቶች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ የአግሮ ኬሚካሎች መጠን ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲገዛና እንዲሰራጭ፣ ግልጽነት ያለው የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያላደረገ፤ እንዲሁም ግብዓቶች በጉምሩክ በኩል እንዲገባ የፈቃድ ወረቀት ከመስጠት ውጪ ያስገቡት ግብአት ከምን ያክል ቆይታ በኋላ አገልግሎት አይሰጥም የሚለውንና የገባውም ግብአት ስለትክክለኛነቱ እንደማያረጋግጡና ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባም ክትትልና ቁጥጥር ያላደረገ መሆኑ ፣
- የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የአወጋገድ መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ በአበባ እርሻ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን እንዲወገድ ባለማድረጉ ድርጅቶቹ ውስጥ ተከማችተው ሳይወገድ ብዙ ጊዜ በመቀመጡ ለአካባቢ፣ ለሰው፣ ለእንስሳትና ለውኃ አካላት ደህንነት አስጊ መሆኑ፤
- በወጣው የአከባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 ዓ.ም ማንኛውም ፕሮጀክት ኢንቨስትመንት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ሁሉም የአከባቢ ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ (ESIA) እንዲያዘጋጁ የሚል አስገዳጅ አዋጅ የወጣ ሲሆን ሁሉም የአበባ እርሻ ድርጅቶች ከ1996 በኋላ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ቢሆንም የአከባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ሳያዘጋጁ ወደ ስራ የገቡ ሲሆን፣ እንዲሁም አንዳንድ የአበባ እርሻ ድርጅቶች ደግሞ የአከባቢ አያያዝ ዕቅድ(Environmental management plan) ማዘጋጀት ሲገባቸው ያላዘጋጁ መሆኑ፣

- አንዳንድ የአበባ እርሻ ድርጅቶች ሀገራዊና እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች፣ የስራ አካባቢ የደህንነት መጠበቂያ ቁሶች፤የጤና ምርመራ ድንጋጌዎች መሰረት አሟልተው እየሰሩ አለመሆናቸው፤
- የደረቅ እና የፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ፣ አከመቻቸት እና አወጋገዱ በተመለከተ የፍሳሽ ማጣሪያ/መከሚያ ቴክኖሎጂዎች ዊትላንድ የማይጠቀሙና እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻን ለማስወገድ ደረቅ ቆሻሻው ከምንጩ ተለይተው በደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎቹ ላይ የጽሁፍ/ምልክት የማይፃፍበት እና ደረቅ ቆሻሻው የሚቃጠልበት የተለየ ቴክኖሎጂ ኢንሲነሬተር(incinerator) የሌለውና ቆሻሻው ግቢ ውስጥ ተጠራቅሞ ክፍት ቦታ ላይ የሚቃጠል መሆኑ፤
- በናሙና ተመርጠው በታዩትና በተከለሱት ማስረጃዎች በተለያዩ የአበባ እርሻ ድርጅቶች 662.8 ሄክታር መሬት ያልለማ ሲሆን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ጠንካራ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ለአልሚዎች (ኩባንያዎች) የተሰጣቸውን መሬት በአግባቡ እንዲጠቀሙና የመሬት ብክነትን ለማስወገድ ክትትልና ድጋፍ አላደረገም፡፡
- የአበባ አልሚ ባለሀብቶች ፈቃድ ሲያወጡ ጀምሮ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት (ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን እንዲሁም ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እና ክልሎች) ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ያልዳበረ መሆኑ፣

ለተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ግብርና ሚኒስቴር በተቀናጀ መልኩ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የአበባ እርሻ ልማት ፈጣን እድገትና ቀጣይነትን ለማረጋገጥ እና በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ያሉትን ችግሮች በማጥናት ስራዉን ሊያግዙና የተሳለጠ የሚያደርጉ የህግ ማእቀፎች (ፖሊሲ፣ መመሪያዎች፣ ስትራቴጂዎች፤ ፍኖተ ካርታ፤ ስታንዳርድ/ጋይድላይኖች እና የኮንሶሊዴሽን የህግ ማዕቀፍ መመሪያ፣ የተቀናጅ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ)፤በማውጣት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ጠንካራና ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

በተጨማሪም የአበባ እርሻ ድርጅቶች በሰራተኛው፤ በአካባቢ በሰው በእንስሳት የአባቢ ደህንነትን ከማረጋገጥ አኳያ (በአፈር፣ በውሃ፣ በብዝሃ ሕይወት በሕብረተሰቡ) ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያደርስ የተከለከሉና ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እንዳይጠቀሙ፤ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የማህበራዊና የአካባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎችን አሟልተዋል ተብሎ የውስጥ እና የውጪ የአካባቢ ኦዲት ሪፖርት ሲቀርብ ስለትክክለኛነቱ ሰርተፍኬት

በሚሰጠው አካል ተረጋግጦ ሰርተፍኬት እንዲሰጥ የድጋፍና የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል።

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የግብርና ዘርፍ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ዘርፉ የሚጠበቅበትን ውጤት ለማሳካት የተነደፉ ሀገራዊ ፖሊስዎችና ስትራቴጂዎች በየአምስት ዓመቱ ተከታታይ የልማት ፕሮግራሞችን እየነደፈ ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡መንግስት ሀገራዊ ለውጡን መነሻ በማድረግ የነበረዉን የኢኮኖሚ እድገት መዋቅራዊ ሽግግርን በሚያመጣ መልኩ ለማስቀጠል በኢኮኖሚ እድገቱ ውስጥ የነበሩ ተግዳሮቶችን በመለየትና በመቅረፍ እና አዳዲስ አገራዊ እድሎችን በማካተት በ2011 ሀገራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ይፋ አድርጓል፡፡
2. የዛሬው የግብርና ሚኒስቴር የተቋቋመው በ1907 ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት የግብርና ገጠር ልማት ሚኒስቴር፤የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ሚኒስቴር፤ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር በሚሉት ስያሜዎች ሲጠራ ቆይቶ አሁን የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባርና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የግብርና ሚኒስቴር በሚል መጠሪያ እሰራ ይገኛል፡፡
3. በኢትዮጵያ አትክልት ፍራፍሬንና አበባን በማልማት ለገበያ የማቅረብ ተግባር በ1974 ዓ.ም. አከባቢ የተጀመረ ስለመሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በተለይም ከዕዝ ኢኮኖሚ ወደ ገበያ መር ኢኮኖሚ ሽግግር ከተደረገ በኋላ የግል እርሻዎች በእጅጉ ተስፋፍተዋል፡፡ የሆርቲካልቸር ዘርፍ በዋነኛነት የሚካተቱት የምርት አይነቶች (አበባና የአበባ ችግኝ፣ ፍራፍሬ፣ አትክልት እና ሽርብስ) ሲሆኑ ባሁኑ ጊዜ ሀገሪቱ በዚህ መጠነ ብዙ መዋዕለንዋይ በሚጠይቅ ዘርፍ በተለይ በአበባ ኤክስፖርት 60 እርሻዎችን በማንቀሳቀስ እጅግ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበች ሲሆን ከኬንያ በመቀጠል ከአፍሪካ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡
4. የግብርናን ዕድገት ለማፋጠንና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ በገበያ የሚመራ የግብርና ስርዓት እውን ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ጥረቶች መካከል ምርታማነትን ማሳደግ፣ ጥራትን መሰረት ያደረገ ምርት ማምረት፣ እንዲሁም ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ቁልፍ ተግባርት ይገኙበታል፡፡

5. የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ግኝት የተመሰረተው በግብርና ምርቶች ላይ በመሆኑ እነዚህን እድሎችን በላቀ ደረጃ ለመጠቀምና ተግዳሮቶችን በዝርዝር በመፈተሽ ደረጃ በደረጃ ለማስወገድ የሚያስችል ስራ መስራትን ታሳቢ አድርጎ እየሰራ ይገኛል፡፡

## የግብርና ሚኒስቴር ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ስልጣንና ተግባር

**ራዕይ**

6. በ 2020 ዓ.ም. የተሻገረ እና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር መሰረት የሚጥል ግብርናን ማየት።

**ተልዕኮ**

7. የግብርናን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ማሳደግ እና የተፈጥሮ ሃብትን መጠበቅና በዘላቂነት መጠቀምን ማረጋገጥ ነዉ፡፡

## የግብርና ሚኒስቴር ስልጣንና ተግባር

8. የግብርና ሚኒስቴር የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2021 መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ፡-

- የግብርና እና የደን ልማትን እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የፖሊስ ትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና የሕግ ማዕቀፎችን ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- የእፅዋት፣ እንሰሳትና ዓሳ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ በዚሁ ረገድ የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮችን ይመራል ያስተባብራል፣
- የእፅዋትና እንስሳት ጤና አገልግሎትን ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል የሚያስችሉ ሥርዓቶችንና መሠረተ ልማቶችን ይዘረጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ላብራቶሪዎችና ክሊኒኮች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ አቅማቸውን ይገነባል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

- የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት ምዝገባና ቁጥጥር ይዘረጋል፣ የምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከሀገር በሚወጡት የእፅዋት ቁጥጥር እና እንሰሳትና የእንሰሳት ተዋጽኦዎች ላይ የኳራንቲን ቁጥጥር ሥራን ያስተባብራል፤
- በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በገበያ የሚመራ የእንስሳት ሀብት ልማት፣ ውሃን ማዕከል ያደረገ የሰብልና የእንስሳት መኖ ልማት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የግጦሽ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ልማት አጠቃቀም ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሠራል፤
- የተፋሰስ፣ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል፤
- ከሚመለካታቸው አካላት ጋር ቅንጅ በመፍጠር የግብርና ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ሥራዎች በአግባቡ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤ ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት አማራጮችንና እምቅ አቅሞችን ይለያል የኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚስፋፉበትን ስልት ይቀይሳል፣
- በዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤
- የግብርናና የሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ትስስር ለማጠናከር ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣ ለዘርፉ አሳታፊና ዘላቂ መዋቅራዊ ለውጥ የሚመጣበትን ስልት ይነድፋል፣ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤የሚሉት ዋናኞቹ ናቸው፡፡ **(ዝርዝሩ በአባሪ-1 ተያይዟል)**

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀትና የሰው ኃይል

### የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት

9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሾሙ አንድ ሚኒስቴር እና አራት ሚኒስተር ዲኤታዎች ያሉት ሲሆን፣ እንዲሁም ለሚንስትሩ ቀጥታ ተጠሪ የሆኑ (የስራ አመራር ዋና ስራ አስፈጻሚ፣የሚኒስቴር ጽ/ቤት ሀላፊ፣የፖሊሲና ስትራቴጂ ጥናት ምርምር መሪ፣የስርዓተ ምግብ እና የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት፣ 9

ተጠሪ ተቋማት ያሉት ሲሆን፤ ለሚኒስትር ዲኤታዎቹ ተጠሪ የሆኑ 16 መሪ ስራ አስፈፃሚ የተደራጀ ነው፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ- 2 ተያይዟል)

**የሰው ኃይል**

10. ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በሲቪል ሰርቪስ በመዋቅሩ የተፈቀደ የስራ መደብ 1101 ሲሆን እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ሴት 347 እና ወንድ 530 በድምሩ 877 ቋሚ ሰራተኞች አሉት፡፡ የሰራተኞቹ የትምህርት ደረጃቸው ሲታይ እንደሚከተለው ነው፡፡

| ተ. ቁ | የትምህርት ደረጃ | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ፒኤችዲ | 4 | - | 4 |
| 2. | ማስተርስ/ የሁለተኛ ዲግሪ | 164 | 52 | 216 |
| 3. | ቢኤ/ቢኤስሲ/ኤልኤልቢ/የመጀመሪያ ዲግሪ | 112 | 99 | 311 |
| 4. | ዲፕሎማ | 20 | 30 | 50 |
| 5. | ሌብል 3 እና 4 | 23 | 42 | 65 |
| 6. | 12ኛ ክፍልና በታች | 107 | 124 | 231 |
| | **ድምር** | **530** | **347** | **877** |

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

11. የግብርና ሚኒስቴር በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለማከናወን ከመንግስት መደበኛ በጀት እና ካፒታል ያለው ሲሆን፤ ከ2012 እስከ ታህሳስ 2015 ዓ.ም ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

**መደበኛ በጀት አፈፃፀም**

| ተ.ቁ | ዓ/ም | የተመደበ መደበኛ በጀት | ስራ ላይ የዋለ | ስራ ላይ ያልዋለ | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2012 | 1,561,859,657.08 | 1,375,050,727.72 | 186,808,929.36 | 88.04% |
| 2 | 2013 | 2,327,087,500.63 | 2,038,788,574.09 | 88,298,926.54 | 87.61% |
| 3 | 2014 | 2,763,41,1218.28 | 2,750,201,409.70 | 13,209,808.58 | 99.52% |
| 4 | እስከ ታህሳስ 30/2015 | 727,253,130.17 | 363,472,995.30 | 363,780,134.87 | 49.97% |

ካፒታል በጀት አፈፃፀም

| ተ.ቁ | ዓ/ም | የተመደበ ካፒታል በጀት | ስራ ላይ የዋለ | ስራ ላይ ያልዋለ | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2012 | 8,300,531,607.48 | 1,105,816,094.96 | 7,194,715,512.52 | 13.32% |
| 2 | 2013 | 5,228,868,152.05 | 517,070,059.67 | 4,711,798,092.38 | 9.89% |
| 3 | 2014 | 1,533,052,708 | 584,197,635.74 | 9,488,550,72.26 | 86.02% |
| | እስከ ታህሳስ 30/2015 | 2,013,616,000 | 846,454,41.38 | 1,929,315,558.62 | 4.20% |

## የኦዲቱ ዓላማ

12. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ምርታማነትና በአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ችግሮች ወይም ክፍተቶች ካሉ ችግሮቹን እና መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ አፈጻጸሙ እንዲሻሻል እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

13. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) "የአበባ እርሻ ልማት ምርታማነትና በአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም" ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

14. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ሥር ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተመረጡ ሲሆን፤ እነሱም፡-

- ግብርና ሚኒስቴር በአበባ እርሻ ልማት ሂደት ውስጥ ምርታማነቱ እና የምርት ግብዓት አያያዝ ስርዓቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ

መልኩ ለመተግበር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱና ተግባራዊነቱን መገምገም፤

- ግብርና ሚኒስቴር የአበባ እርሻ ልማት በሚመረትበት ወቅት በአካባቢው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳደር የክትትል ሥርዓት መኖሩንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም ፣
- ሚ/ር መ/ቤቱ ከአበባ እርሻ ልማት ጋር ተያይዞ የሚመጡትን ማነቆዎች ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን መገምገም፤

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

15. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ ሰላሳ ሁለት (32) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት (በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ፣የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 396/201 ፡የአበባ ልማት ዘርፍ የአሰራር ሥነ - ምግባር ስርዓት 207/2011፡የኢትዮጵያ ሃላፊነት የተሞላ ኢንቨስትመንት እውን ለማድርግ የሚያስችል የአካባቢያዊ እና ማህበራዊ የስነ ምግባር ደንብ፡ የፀረ ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ 674/2010፡የግብርና ዘርፍ የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ፡የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ 299/2002 ናቸው፡፡ በተዘጋጁት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 3 ተያይዘዋል፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

### የኦዲቱ ወሰን


16. ኦዲቱ የተከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን እና አለም አቀፍ የክወኔ አከባቢ የኦዲት እስታንሰዳርዶችን መሰረት በመድረግ ሲሆን፤ ኦዲቱ የሸፈነው ጊዜ

ከ2012-2014 በጀት ዓመታት ውስጥ የአበባ እርሻ ልማት ምርታማነት በአከባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን ጋር በተያያዘ በግብርና ሚኒስቴር የተከናወኑ ሥራዎች ላይ ነው፡፡


**የኦዲቱ ዘዴ**

17. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በግብርና ሚኒስቴር ሲሆን በ5 ባለድርሻ አካላት (የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፤ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤ ጉምሩክ ኮሚሽን፤ የትራንስፖርት ሎጂስቲክ ሚኒስቴር ፤ስራና ክህሎት ሚኒስቴር) በሶስት ክልሎች እና በ11 የአበባ እርሻ ድርጅቶች (አሳላ ፍላወር፣ ኤደን ሮዝ፣ ሳሮን ሮዝ፣ አግሮፋርም፣ ደፕሪም ቢዝነስ፣ ቲናው ቢዝነስ፣ አቢሲኒያ ፍላወር ፣ ብራም፣ ሼር ኢትጵያ፣ ኦምኒ ብሎሰም፣ ጆይቴክ፣ እና ክላቨር)እንዲሁም በ11ም የእርሻው አካባቢ ከሚኖሩ የአካባቢ ማህበረሰብ፡በአበባ እርሻ ድርጅት ውስጥ ለሚሰሩ ሰራተኞች እና ለአበባ እርሻ ድርጅት ሠራተኛ ማህበር ፣ በኦሮሚያ ክልል (የኦሮሚያ የአካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች፣ኢንቨስትመንት ቢሮዎች፣ ሰራተኛና ማህበራዊ ቢሮዎች) በደቡብ ክልል (የደቡብ የአካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች፣ኢንቨስትመንት ቢሮዎች፣ ሰራተኛና ማህበራዊ ቢሮዎች) በሲዳማ ክልል (የሲዳማ የአካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች፣ኢንቨስትመንት ቢሮዎች፣ ሰራተኛና ማህበራዊ ቢሮዎች) ከግል ድርጅት (የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር አምራችና ላኪዎች ማህበር፡ ኮንትሮል ዩንየን) ላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና የመስክ ጉብኝት ቼክሊስት በመሙላት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

## 18. የሆርቲካልቸር ልማት መሪ ስራ አስፈፃሚ ስራ ሂደት የስራ ፍሰት



## 19.ኢንቨስትመንት እና ምርት ግብይት መሪ ሥራ አስፈፃሚ የስራ ፍሰት፡



# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

**ፖሊሲ፣ስትራቴጂ፣ ፍኖተ ካርታ እና ስታንዳርድ ማዘጋጀታቸውን በተመለከተ፡-**

19. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት በአካባቢው እና በመሬት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ እና ዕድገት ለማረጋገጥ የሚረዱ የህግ ማዕቀፎችን ቀርፆ በማፀደቅ ተግባራዊነቱን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

20. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን ማቋቋሚያ የወጣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ 396/2009 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ1 በተሰጠው ሀላፊነት የሆርቲካልቸር (የአበባ ልማት) ኢንቨስትመንትን ፈጣን እድገትና ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ፖሊሲዎችን፡ ስትራቴጂና ህጎችን እንደ አስፈላጊነቱ ባለድርሻ አካለትና ተገልጋዮችን በማሳተፍ ያዘጋጃል፤ ትግበራውንም ይከታተላል እንዲሁም በግብርና 10 ዓመት መሪ ዕቅድ የቀሎችን ሀገሮችን ተሞክሮን በመውሰድ ከፍተኛ ማህበራዊ ፣ኢኮኖሚያ እና አከባቢያዊ ጠቀሜታ መነሻ በማድረግ የሆርቲካልቸር ፖሊሲ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እንዳለበት ሀላፊነት ተሰቶታል፡፡

   - ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፤ የአበባ እርሻ የዘርፉ ግብይት ፈጣን እድገትና ቀጣይነትን ለማረጋገጥ እና በአካባቢው ፣ በመሬት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የሚመራበት የራሱ የሆነ የህግ ማዕቀፎች(ፓሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ፍኖተ-ካርታ) ከ2013 ጀምሮ በረቂቅ ደረጃ እንዳለና ፀድቆ ለአልሚዎች(ለአበባ አምራቾች) ተግባራዊ እንዲያደርጉት ያልተላከ መሆኑ ታውቋል፡፡

19. ጉዳዩን አስመልክቶ የአበባ ዘርፉ ለሚመሩት ለበላይ የስራ ሀላፊዎች ጋር በተደረገ ማጠቃለያ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት ምላሽ ከዚህ ቀድሞ የነበረው የሆልቲካልቸር ዘርፉ ተጠናክሮ በመዋቅር ደረጃ ወጥ ባለመሆኑ ምክንያት በረቂቅ ደረጃ እንዳሉና የፀደቀ ፖሊሲ፡ መመሪያ፣ ስትራቴጂ፣ ሮድ ማፕ፣ ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅተው በስራ ላይ እንዲውሉ አለመደረጉንና የአበባ እርሻ ልማት በአከባቢዉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ እና እድገት ለማረጋገጥ የሚረዱ የሕግ ማዕቀፎችን ቀርጾ

በማጸደቅ ተግባራዊነቱን ሊከታተተል እና ሊቆጣጠር የሚገባው የፌዴራል እና የክልል የአከባቢ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን/እንደሆነና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ እና ትብብር ከማድረግ ያለፈ በህግ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት የሌለው እንደሆነና ለአልሚዎች እንደማንኛዉም የንግድ ተቋም የሚመሩበት የራሳቸዉ የሆነ ስትራቴጂ ያላቸው በመሆኑን ገልጸዋል፡፡

20. በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ የሆርቲከልቸር ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ሮድ ማፕ፣ ስታንዳርድ ረቂቅ የተዘጋጀ ቢሆንም የተሻሻለው የግብርና ገጠር ልማት ፖሊሲ ዉስጥ እንዲካተት ተደርጎ ለሚንስትሮች ም/ቤት የቀረበ እና እስኪ ጸድቅ እየተጠበቀ እንደሆነና በአዲሱ የሚ/ር አወቃቀር ተከትሎ የሆርቲካልቸር ልማት እና ግብይት ስራዎች በዓመታዊ እቅድ ተይዞ በመሰራት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል::
21. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆርቲካልቸር ዘርፉ የሚመራበት መዋቅር ባለመኖሩና ትኩረት ሰጥቶ እንዲወጣና ፀድቆ እንዲተገበር አለማድረጉ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፤
22. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማቱ በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ እና የዘርፉ ግብይት የሚመራበት (ፖሊሲ፣ መመሪያዎች፣ ስትራቴጂዎች፤ሮድ ማፕ፤ ፍኖተ ካርታ) በወቅቱ ባለመፅደቃቸውና ለሚመለከታቸው አስፈጻሚና መ/ቤቶችና ፈጻሚ ድርጅቶች ባለመውረዳቸው የድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥ የተሳለጠ እና አስተማማኝ እንዳይሆንና ከልማቱ ሊገኝ የሚችለውን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ዝቅተኛ እንዲሆን እና በዘርፉ የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በወቅቱና በአፋጣኝ እንዳይፈቱ ወጥነት ያለው የተጠያቂነት ስርዓት እንዳይኖር፤ እንዲሁም የአካባቢ ደኅንነትንና ማሕበራዊና ተጠቃሚነትና ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ሥርዓት እንዳይዘረጋና የአበባ እርሻ ድርጅቶች ሃላፊነታቸውና ሀገራዊ ግዴታቸውን እየተወጡ መስራታቸው ለማረጋገጥ እንዳይቻል አስተዋጽ አድርገዋል፡፡

**የአበባ እርሻ ምርቶች እንዳይበላሹ የኮንሶሊዳሽን የህግ ማዕቀፍ መዘጋጀቱን በተመለከተ ፡**

23. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ምርቶች ብክነት በአካባቢ እና በኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳያስከትሉ የኮንሶሊዴሽን የህግ ማዕቀፍ መመሪያ አውጥቶ ሊያስተገብር ይገባል፡፡

24. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተለለሱ ሰነዶችና በናሙና ተመርጠው በታዩት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ከተገኘ መረጃ የኮንሶሊዴሽን

ህግ ማዕቀፍ፣ አፅድቆ ተገባራዊ ለማድረግ ወደ 7 አመት የፈጀ እንደሆነ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንሶሊዴሽን የህግ ማዕቀፎች ለመተግበር በ2013 በጀት አመት ለመስራት ያቀደ ቢሆንም፤ በዕቅዱ መሰረት ህጉን አውጥቶ፤ አፀድቆ ተግባራዊ እንዳላደገ ታውቋል፡፡

25. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣በረቂቅ ሪፖርት፣ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ በሰጡት መልስ የኮንስለዴሽን መመሪያው ባለመኖሩ ከሆርቲካልቸር ማህበሩ የገጠማቸው ችግር ስላቀረቡልን የህግ ማዕቀፍ ዝግጅቱ የብዙ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎን የሚጠይቅ በመሆኑ ረዥም ጊዜ የወሰደ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ረቂቅ ሰነዱን በማዳበር በዚህ በጀት ዓመት ስራ ላይ ለማዋል ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል ፡፡

26. በሚኒስቴር ቤቱ የሆልቲካልቸር መዋቅር ባለመዘጋጀቱና ስራውን ሊያሰራ በሚያስችል መልኩ ያልተደራጀ እና ለስራው ትኩረት በመስጠት ሕጉ እንዲወጣና ፀድቆ እንዲተገበር አለማድረጉ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

27. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንስለዴሽን የህግ ማዕቀፍ መመሪያ አውጥቶ ባለማስተግበሩ አምራች፣ ገበያ አገናኝ፣ ሻጭና ተጠቃሚ ስለማይገናኙ በግብይት ወቅት ከፍተኛ የሆነ የምርት ብልሽትና ብክነት እንዲከሰት እና የውጪ ንግድና የምርት ተፈላጊነት እንዲቀንስ ከማድረጉም በላይ ሀገሪቱ ከውጭ ንግድ ለማግኘት የሚታቀደውን ገቢ እንዳታገኝ ያደርጋል፡፡

**የአበባ አልሚ ድርጅቶች የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች የሚያደርሱት ተፅጽኖ ላይ ጥናት መደረጉን በተመለከተ፡**

28. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አምራቾች የአበባ እርሻን ለማልማት የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች በተፈጥሮ ሀብት ፣በእፀዋት፣ በእንሰሳት ላይ ስለሚስያከትሉት ችግሮች ጥናቶች እና ምርምሮች ሊያካሂድና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

29. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡

- የአበባ እርሻ ልማት ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚጠቀሟቸው ግብአቶች እንደ ኬሚካል፣ ፍሳሽ ቆሻሻ፣ ተረፈ-ምርት፣ የኬሚካል መያዣ ፕላስቲኮች እና የመሳሰሉት ያለምንም ቅድመ ማጣራት ወደ አካባቢው ማህበረሰብ የሚለቀቁ (የሚጣሉ) በመሆናቸው በድርጅቶቹ አካባቢ በሚኖሩ ሰዎች ላይ ጉዳት

እየደረሰ መሆኑን፣ እንዲሁም መሬታቸው እንደ በፊቱ ምርት እየሰጠ እንዳልሆነና በከብቶቻቸውም ላይ የውርጃ እና ሞት ጉዳት እየተከሰተ መሆኑ፤ ንቦቻቸውም አበባው ላይ የተረጨውን ኬሚካል በመቅሰም መሞታቸው፡ በዝዋይ ሀይቅ ውስጥ የአካባቢ ሰዎች ሲታጠቡና ሲዋኙ ሰውነታቸውን ማሳከክና እንዲሁም የቆዳቸው ቀለም መቀየር እየተከሰተባቸው መሆኑ፣ለአካባቢው ማህበረሰብ በቀረበው ቃለ-መጠይቅ መገለጹ፤

- ከባቱ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በተገኘ መረጃ በባቱ ከተማ የሚገኘው ሼር ኢትዮጵያ ድርጅት የሚወጣው አረንጓዴ ተክሎችና ተረፈ ምርቶች እንስሳት በመመገባቸው ወደ 10 የሚሆኑ ከብቶች ሞተው ድርጅቱ ካሳ እንደከፈለ እና ከዝዋይ ሐይቅ የሚገኘው የዓሳ ምርት/ ቁጥር እየተመናመነ የመጣ መሆኑ፤ የሮሽናራ የአበባ እርሻ፣ እርሻው የኬሚካል ዕቃዎችና የሚረጩ የተለያዩ የፍሳሽ ምንጮች(ከሚረጩ ሰራተኞች መታጠቢያ ክፍል የሚወጣ ፈሳሽ፡ከኬሚካል ጋር ንክኪ ያላቸው ልብሶች ከሚታጠቡበት ገንዳዎች የሚወጣ ፈሳሽ፡ ከአበባው ላይ ከሚረጩት ኬሚካል የሚወርድ ፈሳሽ) ሲኖሩት በባለሙያ የተደገፈ የተቀናጀ የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ ስርዓት ስለማይተገበር፤በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት እና የሀብት ብክነት ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- በተጫማሪም ማጂክ ኢትዮጵያ(EMF PIC) ከድርጅቱ የሚፈሰው ፈሳሽ ከመለቀቁ በፊት በአግባቡ ሳይጣራና ምንም አይነት ምርመራ ሳይደረግ ወደ አካባቢው ወንዝ የሚለቀቅ መሆኑ እየታወቀ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያስጠናው ጥናት እንደሌለ ነገር ግን የአበባ እርሻ ድርጅቶች የስጋት ትንተና (Risk Assessment) የሚሰሩ ቢሆንም ይህንን ማስረጃ በመንተራስ ግብርና ሚንስቴር ግብረ-መልስና አቅጣጫ ያልሰጠ መሆኑ በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሆልቲካልቸር ማህበር ጋር በመሆን የሚጠቀሙትን ተረፈ ምርት መልሶ መጠቀም እንዳለባቸውና የዊትላንድ(የፈሳሽ ቆሻሻ ማስወጋጃ ሲስተም) እንዲጠቀሙ የተደረገ ቢሆንም፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረሰው ጉዳት ምን ይመስላል የሚለውን ጥናት እንዳላደረጉ እና የድጋፍና ክትትል ያልሰሩ፤ በአሁኑ አደረጃጀት ስራው ተጠናክሮ መሄድ ስላለበት በቀጣይ እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

31.እንዲሁም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ የአበባ አልሚ ድርጅቶች የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች የሚያደርሱት ተፅጽኖ ላይ ጥናት የማድርግ እና የመቆጣጠር ተግባር እና ኃለፊነት የፌዴራል እና የክልል የአካባቢ ጥበቃ እና የአየር ንብረት ለውጥ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ሲሆን፤ ሆኖም ሚ/ር የድጋፍ እና ግንዛቤ የመስጠት ስራ በሚ/ር መ/ቤቱ ባለሞያዎች በመስጠት ላይ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

32.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባን ኢንቨስትመንት በባለይነት እንዲያስተዳድር በተሰጠው ሀለፊነት መሰረት ኢንቨስትመንት ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ሊያስከትል የሚችለውን ችግር መርምሮ ከወዲሁ የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያሳይና የመፍተሄ እርምጃዎችን የሚያመለክት ጥናት (pre-feasibility study) አሰራር ተዘርግቶለት ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት በሚኒስቴር መ/ቤቱ 10 አመት መሪ ዕቅድ ገጽ 51 ላይ የተቀመጠ በመሆኑ የአበባ እርሻ ለማልማት የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች በተፈጥሮ ሀብት፣በእፀዋት፣ በእንሰሳት ላይ ችግር ማምጣቱን ጥናቶች እና ምርምሮች አካሂዶ የመፍተሄ እርምጃዎችን ባለመውሰዱ ይህን የመቆጣጠር ተግባር እና ኃላፊነት የፌዴራል እና ክልል የአካባቢ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን/ቢሮ ነው ብሎ የተሰጠው ምላሽ እንዲሁም የድጋፍ እና ግንዛቤ የመስጠት ስራ የሰሩበት ማስረጃ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ስላልቀረበ የተሰጠውን ምልሽ ለመቀበል ይቸግራል፡፡

33. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባን ልማት ዘርፍ የሚመሩት የበላይ የስራ ኃላፊዎች ለስራው ትኩረት ባለመስጠታቸውና በዘርፉ ያሉት ባለሙያዎች በዕቅዳቸው ውስጥ አካተው የድጋፍና የክትትል ስርአት ዘርግተው ባለመስራታቸው ችግሩን በጥልቀት እንዳይረዱት ማድረጉ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

34. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አጋርነትን በመፍጠር የአበባ እርሻ ለማልማት የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች በተፈጥሮ ሀብት ፣በእፀዋት፣ በእንሰሳት ችግር ማምጣቱን በጥናት ላይ የተመሠረተ ሥራ ባለመስራቱ የሚፈጠረው ችግር በመረጃ አውቆ ችግሩን በዘላቂነት ባለመቅረፉ በአካባቢ፣ በሰው እና በእንሰሳት ላይ ከዚህ በላይ የተገለጹትን አሉታዊ ተፅጽኖ እያስከተለ ይገኛል፡፡

**የአበባ እርሻ ልማት የሚጠቀሙት ኬሚካሎች አያያዝ እና የአወጋገድ መመሪያ መዘጋጀቱን በተመለከተ፤**

35. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማቱ የሚጠቀሙት ኬሚካሎች በተገቢው መንገድ ስለመጓጓዛቸው እና በተገቢው መጋዘኖች ውስጥ ስለመከማቸታቸው እንዲሁም ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የአወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊነቱን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

36. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የአወጋገድ መመሪያ ያላዘጋጀ ሲሆን፤ የአበባ አልሚ ድርጅቶች የሚጠቀሙትን ኬሚካሎች ሥርዓት ባለው መልኩ ስለማጓጓዛቸው በተገቢው የመጋዘን አቀማመጥ ስለማስቀመጣቸው ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለዓብነትም፡-


- ሳታሳይ plc ደረቅ ቆሻሻዎችን የማቃጠያ የተለየ ቦታ የሌለው ሲሆን ኬሚካል አዘል የተለያዩ ፈሳሾችን በአንድ ጉድጓድ ዉስጥ በማጠራቀም እዛው የሚቀር መሆኑንና የኬሚካል አቀማመጡ የተዝረከረከና ፍሳሽ ኬሚካሎች ከጠጣር ኬሚካል ጋር ተቀላቅሎ የሚቀመጥ መሆኑ ፤




ፎቶ 1፡የሳታሳይ plc ኬሚካል አቀማመጡ እና የኬሚላል አዘል ቆሻሻ አጣጣል

- ኦምኒ ብሎሶም ድርጅቱ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የኬሚካል ማከማቻ መጋዘን የሌለውና ፈሳሽ ኬሚካሎቹ ከሌሎች ወይም ጠጣር ኬሚካሎች ጋር ተቀላቅሎ መለያ ምልክት ያልተደረገላቸውና ፈሳሽ ኬሚካሎች በመደርደሪያ ላይ መፍሰስና ከሌሎች ኬሚካሎች ጋር ንክኪ መፍጠር እንዲሁም ማከማቻ ቦታው ጠባብና ለአየር ዝውውር ምቹ አለመሆኑና ምንም አይነት ቬንትሌተር የሌለውና መጋዘኑ ቢያንስ 50 ሜትር ከፍሳሽ ቆሻሻ

ማጠራቀሚያ ጉድጓድ ያልራቀ እና ሌሎችም ጥቅም ላይ የማይውሉ ቆሻሻዎች ተከማችተው መኖራቸው፣



ፎቶ 2፡ ኦምኒ ብሎሶም ኬሚካሉ እየፍሰሰ መሆኑ

- ቤቲ ኦርናሜንታል ፕላንትስ ኃላ/የተ/የግ/ማ የኬሚካል መጋዘኑ በጣም ጠባብና በቂ የአየር ዝውውር የሌለው መሆኑ፣ ጊዜ ያለፈባቸዉ ኬሚካሎችንና ኬሚካል ከውስጡ ያለቀ ባዶ ፕላስቲኮች በዛዉ መጋዘን ዉስጥ መከማቸቱ እና የማዳበሪያ መጋዘኑ ኮንቴይነር በመሆኑ ከፍተኛ ሙቀት ያለዉና በቂ የአየር ዝዉዉር የሌለዉ መሆኑ፤
- በተጨማሪም ክላቨር ፍላወር መጋዘኑ በቂ የሆነ የአየር ዝውውርና ቬንቲሌተር የሌለው ሲሆን ኬሚካሉም እስታንዳርዱን በጠበቀ መልኩ ያልተቀመጠ መሆኑ (ማለትም ጠጣርና ፍሳሽ ኬሚካል በአንድ ላይ መቀመጣቸው) እንዲሁም ኬሚካሉ ሲጓጓዝ ተገቢና ምቹ ባልሆኑ መኪኖች የሚጓጓዝ መሆኑ፣




ፎቶ- 3 ክላሽር ፍላወር ፈሳሽ ኬሚካሉ ከጠጣር ጋር ተቀላቅሎ መቀመጡ

- አሮው ኤክስፖርት የአበባ እርሻ ድርጅት የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጋዘኑ በቂ የአየር ዝውውር የሌለው እንዲሁም የኬሚካል አቀማመጡ ጊዜ ያለፈባቸውና ያላለፈባቸው ኬሚካሎች በአንድ ላይ ተቀላቅለው በኬሚካል ማከማቻ ግምጃ ቤት ውስጥ መገኘቱ፤ አቢሲኒያ ፍላወር ሃ/የ/የግ/ማ ማከማቻ መጋዘኑ 50 ሜትር ከፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ የራቀ ሆኖ መገንባት ያለበት ቢሆንም ከጉድጓድ አጠገብ ያለ መሆኑ፣ በተጨማሪም ሮሽናራ የአበባ እርሻ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከማዳበሪያ መቀላቀያ ክፍል (Fertigation room) እንዲሁም ከአፈር ውጪ ያለ ንጥረ ነገር ምግብ ውህዶች ውስጥ በማሳደግ ስርአት (Hydroponic System) የሚወጣው የማዳበሪያ ፍሳሽ አያያዝ ስርዓት በአከባቢ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት እንዳይኖር በሚያስችል መልኩ ተግባራዊ ያላደረገ ሲሆን ከላይ ከተጠቀሱት የአበባ አልሚ ድርጅቶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የአበባ ምርቶች በተገቢው መንገድ ስለማጓጓዛቸው ስለማከማቸታቸው ድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑን፤

  በኦዲቱ ወቅት በተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በሌላ መልኩ ደግሞ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጊዜው ያለፈባቸው እና የተከለከሉ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የአወጋገድ መመሪያ ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ያላዘጋጀ በመሆኑ በአበባ እርሻ ድርጅቶ ውስጥ የሚገኙ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ሳይወገዱ ብዙ ጊዜ በመቀመጡ

ለአከባቢ፣ለሰው፣ ለእንስሳትና ለውኃ አካላት ደህንነት አስጊ መሆኑ፤(የቢጫው ሀሳብ በዚኛው ቢተካ ወይም ቢቀየር)

- እንዲሁም ግብርና ዘርፍ መሪ ዕቅድ በየምርት ወቅቱ የሚፈለገው የአግሮ ኬሚካሎች መጠን ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲገዛና እንዲሰራጭ ተገቢው ክትትል ይደረጋል የሚል ቢሆንም፤ የአበባ እርሻ ድርጅቶች ከውጭ በብዛት ስለሚያስገቡ ለጊዜው ከሚጠቀሙት ኬሚካል ከመጠን በላይ በመሆኑ ጊዜው ያለፈበት ኬሚካል በየእርሻ ድርጅቶቹ ተከማችቶ መኖሩ ግብርና ሚኒስቴር ይህንንም ስለመከታተሉ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

37. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የኬሚካል ማከማቸቱ ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳለና መጋዘኑን ደፍረው ገበተው ድጋፍና ክትትል ያላደረጉ እንደሆነና በቀጣይ እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

38. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ይህን የመቆጣጠር ተግባር እና ኃላፊነት የፌዴራል እና ክልል የአከባቢ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን/ቢሮ ሲሆን ግንዛቤ የመስጠት ስራ ግን በተደጋጋሚ በሚ/ር መ/ቤቱ ባለሞያዎች ሲሰጥ እንደነበረ ገልጸዋል፡፡

39. በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኬሚካሎችን ስለማጓጓዝና ስለማከመቸት ብቻ ሳይሆን ስለአጠቃቀምና ባዶ የኬሚካል ዕቃዎች አወጋገድን በተመለከተ ሳይንሳዊ ዕውቀትን መሰረት በማድረግ ድጋፍና ክትትል ስራ ይሰራል፡ በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያየ ጊዜ ለአበባ እርሻዎች ስራዎችን የግንዛቤ የመስጠት ስራ ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በግብርና ሚ/ር አዲሱ መዋቅር የግብርናን የአካባቢና ማህበራዊ ጥበቃ ጉዳዮችን የሚከታተል እንደገና የመከለስ ስራ በመስራት በተጠናከረ መልክ መስራት ያስፈልጋል በሚል ገልጸዋል።

40. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ማከማቸቱ ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳለና መጋዘኑን ደፍረው ገበተው ድጋፍና ክትትል እንዳላደረጉ፤በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ይህን የመቆጣጠር ተግባር እና ኃላፊነት የፌዴራል እና ክልል አከባቢ ጥበቃ እንደሆነ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ ኬሚካሎችን ስለማጓጓዝና ስለማከመቸት ድጋፍና ክትትል ስራ ሲሳራ እንደነበርና ለአበባ

እርሻዎች ስራዎችን ግንዛቤ የመስጠት ስራ ሲያከናውን እንደቆዩ የገለጹ ሲሆን የሰጡት ምላሽ አንደኛው ከሌላኛው እርስ በርሱ የሚጣረዝና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው የአካባቢያዊ እና ማህበራዊ የስነ ምግባር ደንብ መሰረት የአበባ አልሚ ድርጅቶች የሚጠቀሙትን ኬሚካሎች ሥርዓት ባለው መልኩ ስለመጓጓዛቸውና አቀማመጡ በተገቢው መጋዘን ውስጥ ማከማቸት እንዳለበት በደንቡ የተቀመጠ በመሆኑ የአከባቢ ጥበቃ ሀላፊነት ነው ተብሎ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የሌለውና ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክትትል ስራ ስለመስራታቸው የሚያሳይ ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ስላልቀረበ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ይቸግራል፡፡

41. የአበባ ዘርፉን የሚመሩት የባላይ ሀላፊዎች በአከባቢያዊ እና ማህበራዊ የስነ ምግባር ደንብ መሰረት ኬሚካሉን በተገቢው መንገድ ማስቀመጣቸው እና በተገቢው መጋዘን ማከማቸታቸው የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ባለመከታተሉ እና ዘርፉን የሚመሩት የበላይ የስራ ሀላፊዎች የፀረ-ተባይ አወጋገድ መመሪያ አፀድቆ ተግባራዊ እንዲሆን የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካለትን በተደጋገሚ ተገናኝቶ ውይይት ለማድረግ አጽኖት ሰጥቶት ተከታትሎ እንዲጸድቅ አለማድረጉ እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡
42. የአበባ እርሻ ድርጅቶች የሚጠቀሙት ኬሚካሎች በተገቢው መንገድ ባለመያዙና የአወጋገድ መመሪያው ባለመኖሩ ተከማችቶ ያሉት ኬሚካሎች በወቅቱ ባለመወገዳቸው የፀረ ተባይ ኬሚካሉ በሰራተኛና በእንሰሳትና በአካባቢው እንዲሁም አየር በመበከል ተጽዕኖ ቢያደርስባቸውም አማራጭ በማጣት በቅርበት አብረው የሚኖሩበት ሁኔታ እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡

**የአበባ እርሻ የሚጠቀሟቸዉን ግብዓቶች እና ተረፈ ምርቶች ምርመራ የሚደረግበት የላብራቶሪ ማዕከል ስለመዘርጋቱ በተመለከተ፤**

43. ሚ/ር መ/ቤቱ ለአበባ እርሻ ልማት እድገትና ተደራሽነቱን ለማሻሻል በዘርፉ ላይ የሚጠቀሟቸዉን ግብዓቶች፣የአበባ ምርቶችና ተረፈ ምርቶች ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የላቦራቶሪ ማዕከል ሊገነባና የአበባ አልሚዎችም ላቦራቶሪ ምርመራ ስለመዘርጋታቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
44. አዋጅ ቁጥር 1263/2014/አንቀጽ 20/1/ሰ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአበባ እርሻ ልማት እድገትና ተደራሽነቱን ለማሻሻል በዘርፉ ላይ የሚጠቀሟቸዉን ግብዓቶች፣የአበባ ምርቶችና ተረፈ ምርቶች ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የላቦራቶሪ ማዕከል ሊዘረጋና

የአበባ አልሚዎቹም ላቦራቶሪ ስለመኖራቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ እንደሚገባ ያትታል፡፡

45. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልል ቢሮዎችና ከአበባ እርሻ ድርጅቶች ከተሰበሰበ ማስረጃ የአበባ እርሻ ድርጅቶች በአበባው ላይም ሆነ ተረፈ ምርቶች ላይ ያለው የኬሚካል መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ የሚመረመርበት ቴክኖሎጂ እና ላብራቶሪ ሀገራችን የሌለ ሲሆን፤ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል በአበባውም ሆነ ተረፈ ምርቶች ላይ ያለው ኬሚካል መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ የሚመረመርበት የላብራቶሪ ምርመራ ማዕከሉ እንዲገነባ ያላደረገ እና አበባ አልሚ ድርጅቶችም የራሳቸው እንዲኖራቸው ክትትል እና ቁጥጥር እንዳላደረገ ታውቋል፡፡ ለዓብነትም፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኤክስፖርትና በከፍተኛ ደረጃ ፀረ-ተባይ በሚረጭባቸው አካባቢዎች ላይ የፀረ-ተባይ ቅሪት ምርመራ ማከናወን፤ እንዲሁም በተመረጡ ፀረ ተባዮች ላይ የጥራት ምርመራ ለማድረግ በ2014 በጀት ዓመት ያቀደ ቢሆንም በእቅዱ መሰረት ያላከናወነ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2014 የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎች ፤ፀረ ተባይ አስመጪዎች፣ አከፋፋዮች፣ ቸርቻሪዎች እና ተጠቃሚዎች፣ የሙከራ አገልግሎት የምርምር ማዕከላት ላይ ድጋፍ ፣ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ያቀደ ቢሆንም አፈፃፀሙ 29 % ብቻ መሆኑ፤
- ሳሚ ፍላውር፣ አግሪ ፍሎራ፣ ካፍ ሮዝ፣ አለምዬ አግሪካልቸር፣ ሜትሮሊክስ ፍለወር፣ ድሬ ሀይላንድ፣ ድሬ ባይከለር ፣ መናገሻ ፍላወር፣ ቶፕ ፍላወር/ቢኮ፣ ጆኦ ፍለወር፣ ሱፐራ ፊሎሪቲች፣ አስክ ፍላውር ከአበባ እርሻ ልማት ወደ ሌላ ምርት ኢንጆሪ ሀርበስ በሚቀይሩበት ጊዜ በመሬቱ ላይ ማምረት እንደሚችሉ የአፈር ናሙና ወስደው እና አስመርምረው በሚመለከተው አካል ፍቃድ ሳይሰጣቸው ምርቱን ቀይረው እየሰሩ መሆናቸው፤

46.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት መልስ ከአበባ እርሻ ወደ ሌላ ዘርፍ ሲቀይሩ ምርመራ አድርገው ወደ ሌላ ምርት እንደማይቀይሩና የቅሬት ምርመራ የሚደረግበት ላብራቶሪ ስለሌለ አብዛኛዎቹ እርሻዎች ውጭ ሀገር

ልከው ምርመራ እንደሚካሂዱና እንደ ሀገር ፋይቶሳኒተሪ ምርመራ ለማቋቋም ታቅዶ ዲዛይን ላይ ያለ እንደሆነና ለሚ/ር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆነ የግብርና ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 509/2022 በአዲስ መልክ በቅርቡ የተቋቋመ በመሆኑ ይህ ተግባር ቀደም ሲልም ጅምር ስራዎች ያሉት ቢሆንም በተጠናከረ መልኩ ወደ ፊት እንደሚሰራ ገልጸዋል።

47. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለስራው ትኩረት ሰጥቶ የሚመለከታቸው አካላት አስተባብሮ የላብራቶሪ ምርመራ ማዕከሉ እንዲኖር ጠንከር ያለ የክትትል አድርጎ አለመስራቱ ለግኝቱ እንደ ምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡

48. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የፀረ-ተባይ ቅሪት መጠን ለመለየት የሚያስችል አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ ባለመኖሩና ተግባራዊ ባለመደረጉ በሀገሪቱ ውስጥ በሚመረቱ እና ወደ ውጭ ሀገራት በሚላኩ የአበባ ምርቶች ላይ የፀረ ተባይ ኬሚካል ቅሪት ቢኖር/ቢገኝ ሀገሪቱ በከፍተኛ ወጪ ያመረተችው ምርት እንዲወገድና በውጭ ሀገራት ምርቱ ተቀባይነትና ተፈላጊነቱ እንዲቀንስና በኤክስፓርቱ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

**በአበባ ልማት ዘርፍ የሚከሰቱት ማነቆዎችን ለመፍታት ጥናት መካሄዱን በተመለከተ፤**

49. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ ልማት ዘርፍ የሚከሰቱት ማነቆዎችን ለመፍታት ጥናቶችን በማካሄድ ጥናቱ ያመጣውን ለውጥ የሚገመግምበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

50. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ ልማት ዘርፍ የሚከሰቱት ማነቆዎችን ለመፍታት ከሚመለከተቸው ባለ-ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ችግሮቹን ማለትም የቅዝቃዜ ሰንሰለት((cool of chain) የኤሌክትሪክ አቅርቦት፣የሎጂሰቲክ አቅርቦት ከመከሰታቸው በፊት እና ከተከስተ በኋላ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ያስጠናው ጥናት አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት ሰነዶችና በናሙና ተመርጠው መረጃ ከተሰበሰበባቸው የአበባ አልሚ ድርጅቶች፣ እንዲሁም ከፌደራልና ክልል ባለድርሻ አካላት ታውቋል፡፡ ለዓብነትም፤

- በአበባ እርሻ ልማት ክላስተሮች በየወቅቱ በሚከሰተው የሃይል አቅርቦት ችግር (የሀይል መቆራረጥ፣ የሃይል ማነስ፣ የትራንስፎርመር ፍላጎት ፈጥኖ ምላሽ ያለማግኘት ችግር) እንዲሁም የስልክና የኢንትርኔት አውታሮች ቢዘረጉም በተሟላ መልኩ አገልግሎት እየሰጠ እንዳልሆነና ከፍተኛ የድህረ

ምርት ብክነትን የሚያስከትሉ ችግሮችን ለመፍታት/ለመቀነስ የሚያስችሉ የምርምር ውጤት የሆኑ ቴክኖሎጂዎች አለመኖር፥እና

- ከአበባ እርሻ ልማት ኩባንያዎች(ሼር ኢትዮጵያ፣ ኤኪው፣ዝዋይ ሮዝ፣ ፣ብራም፣ ሀርበርግ) ትላላልቅ ኩባኒያ እንደመሆናቸው መጠን የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ውል የሌላቸው (የሊዝ ስምምነት ተፈጽሞና ካርታ ተሰርቶ መሬቱ በባለቤትነት ለባለሀብቶች ያልተላለፈ) በመሆኑ እርሻውን ለማስፋፋትም ሆነ ከባንክ ብድር ለመበደር ያልቻሉ መሆኑ እንደ ማሳያ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
- በሌላ በኩል ሼር ኢትዮጵያ የቅዝቃዜ ሰንሰለትን የሚያስጠብቅ የሎጂስቲክስ አገልግሎትን በራሳቸውና እና ከሆርቲካልቸር አምራች ላኪዎች ማህበር ጋር በመሆን እያመቻቹ እንዳሉና በግብርና ሚኒስቴር/መ/ቤቱ የቅዝቃዛ ሰንሰለትን የሚያስጠብቅ የሎጂስቲክስ አገልግሎትን እንዲያገኙ ያላመቻቸላቸው መሆኑ ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገራችን የሆነ የምርት ምልክት (Product Branding) በመቅረጽ፣ በማስተዋወቅ፣የመደራደር አቅምን በማሳደግ እንዲሁም በዳግም ኤክስፖርት (Re-export) እየተስተናገዱ ላሉት ደንበኞች (End user customers) ምርቱ በቀጥታ የሚቀርብበት ሁኔታን የማመቻቸት ስራ ቅድሚያ ለማስራት ያቀደ ቢሆንም፤ በዕቅዱ መሰረት ያላከናወነ መሆኑ፣
- እንዲሁም ከትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የአበባ እርሻ ምርታቸውን ጥራቱን ጠብቆ ወደ ውጪ እንዲላክ ከመነሻ(Initial) እስከ መድረሻ (destination) ድረስ የአበባ ምርቱ ሳይበላሽ እንዲቆይ ምርቱ የሚጓጓዝበት የቅዝቃዜ ሰንሰለት (cool of chain) እስካሁን በተደራጀ መልኩ ያልተዘረጋና ሚኒስቴር መ/ቤቱ የድጋፍና የክትትል ያልሰራ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡት ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

51.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ ማነቆዎችን የመለየት ስራ ያለ ቢሆንም፤ በሰነድ መልክ ተሰንዶ የተቀመጠ ማስረጃ (ሰነድ) እንደሌለና ጥናቱ ተቀናጅቶ የተጠና ሳይሆን በኢንቨስትመንት ዘርፍ /ዳይሬክቶሬት ደረጃ ብቻ ጥናቱ እንደተጠና የባለድርሻ አካላት ፎረም ስለተቋቋመ የተጠቀሱት ችግሮችን በየወሩ በሚካሄድ መድረክ እየተፈታ እንደሚሄድና ሆኖም እንደ ሀገር

የመሰረተ ልማት ያለመስፋፋት እና እጥረት እንዳለ ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ ገልጸዋል።

52. የበላይ ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ በ2015 የአበባ እርሻዎች የጎርፍ አደጋን ለመከላከል እንዲሁም ችግሩን በዘላቂነት እንዴት መቀረፍ እንዳለበት ጥናት ያካሄዱት (ማስረጃ)የቀረበ ቢሆንም የአበባው ዘርፍ ሰፊ በመሆኑና ማነቆዎቹ እንዳይከሰቱ ትኩረት ተሰቶት በቀጣይነት ሌሎችንም ማነቆዋችን በማጥናት ስላለበት የአበባ እርሻ ድርጅቶች ካለበቸው ችግር አንጻር ጥናቱ በቂ ነው ብሎ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

53. የአበባ ዘርፉ ተጠናክሮ የሚመለከተውን ባለድርሻ አካላት ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ መፈታት ያለበት ችግር እንዲፈታ በዕቅድ ተይዞ በተከታታነት (ወጥ በሆነ መልኩ) የክትትል ስርዓት ዘርግቶ አለመስራቱ እንደምክንያት ይጠቀሳል፡፡

54. በመሆኑም በአበባ ልማት ዘርፍ የሚከሰቱት ማነቆዎችን ለመፍታት ጥናቶችን ባለማካሄዱና ጥናቱ ያመጣውን ለውጥ የሚገመግምበት ስርዓት ባለመዘርጋቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶቹ ማምረት ያለባቸውን ያክል ምርት አምርተው ለገበያ ስለማያቀርቡ ድርጅቶቹም ትርፋማ እንዳይሆኑና ሀገሪቷ ማግኘት ያለባትን ገቢ እና የውጪ ምንዛሬ እንዳታገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤**

55. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

56. የግብርና ዘርፍ የ5 ዓመት የልማት ዕቅድ 2012 ዓ.ም በወጣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ተግባራዊነቱን ሊከታተል እንደሚገባ ይገልጻል፡፡

57. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ እና ከፖሊሲው የሚመነጭ የህግ ማዕቀፍ አዘጋጅቶ ተግባራዊ አለማድረጉን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት ሰነዶችና በናሙና ተመርጠው ከታዩት ባለድርሻ አካላት ለማወቅ ተችሏል፡፡

58. ለማሳያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኢንቨስትመንት፣ ለመኖሪያነት መዋል አለበት የሚለውን በመለየት ኢንቨስትመንቱን ለማስፋፋት ጥያቄ ለሚያቀርቡት ምላሽ

ለማግኘት የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ያላዘጋጀና ተግባራዊነቱን ያልተከታተለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

59. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ እንደሀገር የመሬት አጠቃቀም አዋጅ ፣ የግብርና የገጠር ልማት ፖሊሲ እንዳለና ሁሉን ያቀፈና የተሻሻለ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ እንዲፀድቅ ለምክር ቤት የላኩ እንደሆነና ያልፀደቀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

60. የግብርና ሚኒስቴር ፖሊሲውን እንዲያወጣ ሀላፊነት የተሰጠው ሲሆን፤ ለተግባራዊነቱ ተከታታይነት ያለው ክትትል ባለመድረጉ የአበባ እርሻ መሬት ማስፋፋት ሲፈለግ ረጅም ሂደት መውሰዱ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

61. በመሆኑም የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ባለመኖሩ እና የነበረው የገጠር መሬት ፖሊሲ ብቻ በመሆኑ የትኛውን መሬት ለግብርና እና የትኛውን መሬት ለሌላ ሥራ (ለከተሞች ልማትና ለኢንዱስትሪ) መዋል እንዳለበት እንዲሁም የግብርናውም ቢሆን ስለ ገጠር ግብርና እና ስለከተማው ግብርና ለይቶ ያስቀመጠ የተቀናጀ ፖሊሲ እንዳይኖር አድርጓል፡፡

**በአከባቢ ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት መመሪያዎችን እና ማኑዋሎችን መዘጋጀቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤**

62. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካባቢ ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት የአበባው ዘርፍ የሚመራበት መመሪያዎች፣ማኑዋሎችን በማዘጋጀት የስነ ምግባር ደንቡ አፈፃፀም ብቁ እና ቀልጣፋ ለማድረግ ለባለሀብቶች እና ለክልልሎች ስልጠና በመስጠት ተግራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

63. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ሃላፊነት የተሟላ ኢንቨስትመንት እውን ለማድረግ የሚያስችል የአከባቢያዊ እና ማህበራዊ የስነ ምግባር ደንብ መሰረት መመሪያዎችን፣ማኑዋሎችን በማዘጋጀት የስነ ምግባር ደንቡ አፈፃፀም ብቁ እና ቀልጣፋ ለማድረግ ለባለሀብቶች እና ለክልልሎች ስልጠና በመስጠት ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡

64. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልል ቢሮዎችና ከአበባ እርሻ ድርጅቶች ከተሰበሰበ ማስረጃ ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአከባቢ ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት መመሪያም ሆነ ማኑዋል ተዘጋጅቶ ለአበባ አልሚዎች እንዲተገብሩት ያልተላከና የስነ-ምግባር ደንቡ አፈፃፀም ብቁ እና ቀልጣፋ ለማድረግና ልማቱን ሲያለሙ በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድሩ ለባለሀብቶች እና ለክልሎች የስነ-ምግባር ደንቡን በተመለከተ ስልጠና ያልሰጣቸው መሆኑ፤
- በሌላ በኩል በግብርና ሚኒስቴር መሪ ዕቅድ የአበባ እርሻ ኢንቨስትመንት ረገድ ያሉ ፕሮጀክቶች፤ ድጋፍ ሰጪ ተቋማትና ባለሙያዎች ስለ መልካም እርሻ አተገባበር (GAP- Good Agricultural Practice) ፤የተለያዩ የአለም አቀፍ የገበያ ጥራት መስፈርት ሰርተፍኬቶች (Global GAP, BRC, BSI, ETI, TESCO እና የምርት ሀገር ስሪት የHscode)ገበያው የሚፈልጋቸው ደረጃዎችን እንዲያሟሉ የግንዛቤ ማሳደግ ስራ በቀጣይ የሚከናወን ተግባር ይሆናል የሚል ቢሆንም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስለመስራቱ የሚሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

  ታውቋል፡፡

65.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የባላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ- መጠይቅ፣ በሰጡት ምላሽ መመሪያውም እንደሌለና ክትትልም ያላደረጉ ሲሆን ለወደ ፊት በቀጣይ እንደሚሰሩትና በአዳዲስ ከፍተኛ ቴክኖሎጂ እና ልምድ አንጻር ከውጪ የመጡ ባለሙያዎች በክህሎት የተሻሉ ሲሆን በአሁን ግን የእውቀት ሽግግር ስለተደረገ በኛ ስልጠና እየተሰጠ ይገኛል እንዲሁም በእርሻው ላይ ያሉት ባለሙያዎች በዕውቀት የዳበሩ በመሆናቸው ክትትል እንደሚደረግ እና ለባለሀብት ሰራተኞች የመንግስት ስልጠና መስጠት ግዴታ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

66. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት፤በመውጫ ስብሰባ በተሰጠው ምላሽ የአከባቢ ስነ ምግባር ደንብ ከሆርቲካልቸር ላኪዎች ማህበሩ ጋር በመሆን ቀደም ሲል የተዘጋጀ ሲሆን ግንዛቤ የመስጠት ስራ ከሌሎች ስራዎች ጋር በመደረብ ሲሰጥ ቆይቷል። ሆኖም በቅንጅት ከሌሎች ፌዴራል እና የክልል የአከባቢ ጥበቃ እና የአየር ንብረት ልውጥ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ እና በቅንጅት የሚሰራ እንደነበርና እንዲሁም ዘርፉን ከሚደግፉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ሲሰጥ ቆይቷል። በተጨማሪ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማህበራዊና አካባቢ

ስነ-ምግባር ደንቡን የመላክና ስልጠና ለሁሉም ክልሎች በየጊዜው የመስጠት ስራ ሲሰራ እንደቆየ ገልጸዋል፡፡

67. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በማጠቃለያ ቃለ- መጠይቅ በሰጡት ምላሽ፤ መመሪያውም እንደሌለና ክትትልም እንደላደረጉና ለወደፊት በቀጣይ እንደሚሰሩት፤በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርትና በመውጫ ስብሰባ በተሰጠው ምላሽ የማህበራዊና አካባቢ ስነ-ምግባር ደንቡን የመላክና ስልጠና ለሁሉም ክልሎች በየጊዜው የመስጠት ስራ ሲሰራ እንደቆየ የገለጹ ቢሆንም የተሰጠው ምላሽ እርስ በራሱ አንደኛው ከሌላኛው የሚጣረዝና ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባውጣው የአከባቢያዊ እና ማህበራዊ የስነ ምግባር ደንብ መሰረት መመሪያዎች እና ማኑዋሎች ማዘጋጀት እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም መመሪያዎች እና ማኑዋሎች ያላወጣና እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ (ስልጠና) የተሰጠበት ማስረጃ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ስላልቀረበ የተሰጠውን ምላሽ ኦዲት በድኑ ለመቀበል ይቸግራል፡፡

68. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባውን ዘርፍ እንዲመሩት የተሰጣቸው የበላይ የሥራ ኃላፊዎች ለስራው ትኩረት ባለመስጠቱ የአበባ ዘርፉ የሚመራበት መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ እንዲሆንላቸውና የሚወጣውንም መመሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እንዳይሰጥ መደረጉ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

69. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአከባቢያዊ እና ማህበራዊ የስነ ምግባር ደንብ መሰረት መመሪያዎችን፡ማኖዋሎችን ባለማዘጋጀቱና በተዘጋጀው መመሪያዎች የግንዘቤ ማስጨበጫ ባለመሰጠቱ የአበባ አምራቾች ምርታቸውን ሲያመርቱ በድርጅቱ ለሚሰሩት ሰራተኞችም ሆነ በአከባቢው ማህበረሰብ ላይ ጉዳት እያደረሱ ምርታቸውን እንዲያመርቱ ያደርጋቸዋል፡፡

**የአበባ እርሻ ድርጅቶች የአከባቢ ኦዲት ማስደረጋቸውን በተመለከተ፤**

70. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የውስጥ እና የውጪ የአካባቢ ኦዲት ስለማከናወናቸው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

71. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው ከታዩት የአበባ እርሻ ድርጅቶች በተገኘው ማስረጃ (አሮው ኤክስፖርት፣ማጂካል ፋርም ሃ/የተ/የግ/ማ እንዲሁም (ኦምኒ ብሎሶም ፣ክላቨር እና ሳታሳይ ) የስራ አካባቢ ደህንነትን ከማረጋገጥ አኳያ በአፈር፣ በውሃ፣ በብዝሃ ሕይወት ሀብት ላይ አሉታዊ

ተጽእኖ አለማድረሱን ለማረጋገጥ ድርጅቱ የአከባቢ ኦዲት ምርመራ ስለማድረጋቸው የሚያስረዳ ማስረጃ የሌለና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጣው የአካባቢያዊ እና ማህበራዊ የስነ ምግባር ደንብ መሰረት የአከባቢ ኦዲት እንዲያስደርጉ ድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

72.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በglobal gap(ኦዲት የሚሰራ) ኦዲት እየተደረጉ እንደሆነና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የአከባቢ ኦዲቱን እንዲያሰሩ ድጋፍና ክትትል ያልተደረገ ሲሆን፣ይህ ተግባር የአከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ሃላፊነት ስለሆነ በቀጣይ ከሚመመለከተው አካል ጋር በመሆን ኦዲቱን እንዲያሰሩ የክትትል ስራ እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

73.በረቂቅ ሪፖርትና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ ይህ ተግባር በቀድሞ አጠራር የደንና የአካባቢ አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን በአሁኑ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተግባርና ሃላፊነት እንጂ የሚ/ር መ/ቤቱ ተግባር አይደለም፡፡

74. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በglobal gap(ኦዲት የሚሰራ ) ኦዲት እየተደረጉ እንደሆነና በቀጣይ ከሚመመለከተው አካል ጋር በመሆን ኦዲቱን እንዲያሰሩ የክትትል ስራ እንደሚሰሩ፣በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተግባርና ሃላፊነት እንጂ የሚ/ር መ/ቤቱ ተግባር አይደለም ተብሎ የሰጡት ምላሽ አንዳኛ ከሌላኛው ምላሽ ጋር እርስ በራሱ ያልተባበና (የሚጣረዝ) ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ሃላፊነት የተሞላ ኢንቨስትመንት እውን ለማድርግ የሚያስችል የአከባቢያዊ እና ማህበራዊ የስነ-ምግባር ደንብ በገጽ ቁጥር 87 መሰረት የአበባ እርሻዎች የአከባቢ ኦዲት እንዲስደርጉ ክትትል ማድረግ እንዳለበት የተቀመጠ በመሆኑ ይህ ተግባር የአከባቢ ጥበቃና አየር ንብረት ለውጥ መ/ቤት ተግባርና ሃላፊነት እንጂ የሚ/ር መ/ቤቱ ተግባር አይደለም ተብሎ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡

75. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ ዘርፉን የሚመሩት የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ቀጣይነት ላለው እድገት አለመስራት እና የግብዓት አጠቃቀም ከአከባቢ ማህበረሰቡ እንዲሁም ከተፈጥሮ ህብት ጋር እንዴት አጣጥሞ መሄድ እንዳለበት የውስጥና የውጭ የአካባቢ ኦዲት እንዲሰሩ ድጋፍና ክትትል

አለማድረጉ እና የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች የአከባቢ አስተዳደር ሂደቶች እና የታቀዱ የአፈፃፀም ደረጃዎች የተገመገሙ ባለመሆኑ ከአመት አመት ጉድለቶችን ላይቶ ያለማሻሻል እንደ ምክንያት ይጠቀሳል።

76. በመሆኑም የአከባቢ ኦዲት በሚመለከተው የመንግስት አካል በአከባቢ ላይ ጉዳት ማድረስ አለማድረሱን ግልፅ፣ አስተማማኝ እና እውነተኛ ግምገማ ስለማይደረግ በአከባቢው (የአፈር እና የውሃ አካላት በኬሚካል መመረዝና በውሃው ዉስጥ የሚኖሩ ብዝሃ ህይወቶች መመናመን) ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲፈጠር ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የአፈር ምርመራ በማድረግ የማከም ስራ መስራታቸውን መከታተሉን በተመለከተ፤**

77. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች በየጊዜው የአፈር ምርመራ እና የማከም ስራ ስለማከናወናቸው ሊከታተል ይገባል፡፡

78. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የአበባ እርሻ ድርጅት (አሳላ ፍላወር፣ ኤደን ሮዝ፣ ሳሮን ሮዝ፣ አግሮፋርም፣ ደፐሪም ቢዝነስ፣ ቲናው ቢዝነስ፣ አቢሲኒያ ፍላወር ፣ ብራም፣ ሼር ኢትጵያ፣ ኦምኒ፣ እና ክላቨር) እንዲሁም ከሰነዶች ክለሳ በተገኙ መረጃዎች የአበባ አልሚዎች የሚጠቀሙት ግብአት በአፈር ውስጥ ምን ያህል ንጥረ ነገሮች (Nutrients) በውስጡ አለ የሚለውን ለማየት የአፈር ምርመራ የሚያካሂዱ ቢሆንም የተጠቀሙት ግብአት(ኬሚካል) በአፈር ውስጥ ምን ያክል የኬሚካል ቅሬት እንዳለውና አፈሩ ምን ያህል ተመርዟል ብለው የማከም ስራ እንዲሰሩ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም የማይከታተል ስለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

79. ለዓብነትም(አሳላ ፍላወር፣ ኤደን ሮዝ፣ ሳሮን ሮዝ፣ አግሮፋርም፣ ደፐሪም ቢዝነስ፣ ቲናው ቢዝነስ፣ አቢሲኒያ ፍላወር ፣ ብራም፣ ሼር ኢትጵያ፣ ኦምኒ፣ እና ክላቨር) አበባ አልሚ ድርጅቶች ምርታቸውን ሲያለሙ የሚጠቀሙት ግብአት ወደ ከርሰ ምድር ውስጥ እንዳይገባ የፕላስቲክ ንጣፍ የማይጠቀሙ ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱም በኩል የድጋፍና የክትትል ስራ ያልሰራ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡




**ፎቶ-4 ከላይ የተገለጹት 11ም የፕላስቲክ ንጣፍ የሌላቸውና የፎቶ 4 ላይ ያለው ምሳሌ ግን (የአስላ) የአበባ እርሻ መሆኑ፡**

80.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ፣በሰጡት ምላሽ የአበባ እርሻ ድርጅቶች በዚህ መልክ ስራቸውን እንዲሰሩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተደረገ ክትትልና ቁጥጥር እንደሌለና ለወደፊት እንደሚያስተካክሉ ገልጸዋል ፡፡

81.እንዲሁም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ይህ ተግባር የአካባቢ ጥበቃና አየር ንብረት ለውጥ መ/ቤት ተግባርና ሃላፊነት እንጂ የሚ/ር መ/ቤቱ ተግባር እንዳልሆነና የሚኒስትር መ/ቤቱ ስራ የድጋፍ፣ ክትትልና የማብቃት በመሆኑና ለወደፊት ከተቆጣጣሪ አካል ጋር ማለትም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር ትኩረት ሰጥቶ ሰፊ ስራ መስራትን እንደሚጠይቅ ገልጸዋል፡፡

82.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በግብርና ሚኒስቴር 10 አመት መሪ ዕቅድ ውስጥ የአፈር ምርመራ እንዲደረግና የአፈር ለምነትን በማሻሻል ምርታመነትን ማሳደግ እንዳለበት ያስቀመጠ በመሆኑ የአበባ እርሻ ድርጅቶች በየጊዜው የመሬት ምርመራ እና ማከም ስራ እንዲያከናውኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ያለበት ቢሆንም ይህ ተግባር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተግባርና ሃላፊነት እንጂ የሚ/ር መ/ቤቱ ተግባር አይደለም ተብሎ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡

83. በመሆኑም የአበባ ዘርፉን የሚመሩት የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች የሚጠቀሙት ግብአት በአፈር ላይ ምን ጉዳት ያስከትላል ብለው ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደረጉ የፕላስቲክ ንጣፉን ማድረግ በአስገዳጅነት እንዲጠቀሙ

የክትትልም ሆነ የድጋፍ ስራ ባለመስራቱ እና ጉዳዩን የሌላ አካል አድርጎ መመልከቱ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

84. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የሚጠቀሙትን ግብአት ወደ ከርሰ ምድር ውስጥ እንዳይገባ የፕላስቲክ ንጣፍ ባለመጠቀማቸው ምርቱን ለማምረት የተጠቀሙት ግብአት ወደ አፈር ስለሚገባ የከረሰ ምድርን ውሀ ከመበከሉም ባሻገር በአፈሩ ላይ ሌላ ምርት ማምረት ሲፈለግ ምርመራ ሳይደረግ ምርቱ ከተመረተበት በአለም አቀፍ ገበያ ምርቱ ተቀባይነት እንዳይኖረው በማድረግ ሀገሪቷ ማግኘት ያለባትን የውጪ ምንዛሬ እንዳታገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የመሬት ልየታ በማድረግ እንዲሰጥ ማድረጉን በተመለከተ፤**

85. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአበባ እርሻ እና ለሌሎች እርሻ የሚውለው መሬት ልየታበማካሄድ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይገባል፡፡

86. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው ከታዩት የአበባ እርሻ ድርጅቶች በተገኘው ማስረጃ ከሚመለከታቸው አካል ጋር በመተባበር ለሆልቲካልቸር የሚሆን መሬት በጥናት ተለይቶ መሰጠት ያለበት ቢሆንም፤

   - አምስት የአባበ ልማት ድርጅቶች (ኦምኒ ብሎሶም ፣ክላቨር፣ በራም፣ሼር ኢትዮጵያ እና ጆይቴክ፣) የተሰጣቸው መሬት ለሌሎች እርሻ ስራዎች የሚውል መሆን አለመሆኑን ሳይለይ የተሰጣቸው እንደሆነና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአበባ እርሻ እና ለሌሎች እርሻ የሚውለው መሬት ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በጥናት ለይቶ ለአልሚ አካላት እንዲሰጥ ድጋፍና ክትትል አለማድረጉ፤ ታውቋል፡፡
   - በሌላ በኩል ከኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ኢንቨስትመንት ቢሮ ለመረዳት እንደተቻለው በአብዛኛው ባለሀብቱ/የአበባ አልሚዎች የሚፈልጉት የካሳ ክፍያ የሌለው መሬትና የለማ(መንገድ አካባቢ፣ ውሃ ያለበት) እና የመንግስት እርሻ የነበሩ ቦታዎች እንደተሰጣቸውና በመሬት ባንክ ተለይቶ የተሰጣቸው መሬት አለመኖሩ ገልጸዋል፡፡

87. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በሰጡት መልስ ለሆልቲካልቸር የሚሆን መሬት በጥናት በመለየት የመስጠት ስራ ያልተሰራ እንደሆነና በቀጣይ ለአበባ እርሻ የሚሆኑ መሬቶችን ከክልሎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እንደሚለዩና ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ለመስራት በሂደት ላይ

እንዳሉ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በጥናት መሬትን የመለየት ስራ እንደተጀመረ ገልጸዋል ፡፡

88.እንዲሁም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ተግባሩ የፌደራል እና የክልል አከባቢ ጥበቃ ሲሆን በሚ/ር መ/ቤቱ ቀደም ሲል የነበረዉ የግብርና አካባቢ ጥበቃ መዋቅር እንዲፈርስ በመደረጉ ተቀናጅቶ ለመስራት አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ገልጸዋል፡፡

89.በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ ለአበባ እርሻ ልማት የሚውል መሬት ልየታ በተመለከተ በህገ መንግሥት እና በኢንቨስትመንት አዋጅ 1180/2012 የተሰጠው ለፌዴራል ኢንቨሰትመንት ኮሚሽን እና ለክልል መንግስታት ነው፡፡

90.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ የስራ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ ምላሽ  መሬቱን በጥናት በመለየት የመስጠት ስራ ያልተሰራ እንደሆነና በቀጣይ ከክልሎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እንደሚለዩ የገለጹ ሲሆን ፤በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ግን በሚ/ር መ/ቤቱ ቀደም ሲል የነበረዉ የግብርና አካባቢ ጥበቃ መዋቅር እንዲፈርስ በመደረጉ ተቀናጅቶ ለመስራት አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ መሬት ልየታ በተመለከተ በህገ መንግሥት እና በኢንቨስትመንት አዋጅ 1180/2012 የተሰጠው ለፌዴራል ኢንቨሰትመንት ኮሚሽን እና ለክልል መንግስታት ነው በማለት መልሷል፡፡ ሆኖም በሶስቱም ጊዜ የሰጡት ምላሽ አንዳኛው ከሌላኛው ምላሽ እርስ በራሱ የሚጣረዝና ሲሆን በደንብ ቁጥር 457/2012 ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተሰቶት የነበሩ የሆርቲካልቸር ሥልጣንና ተግባራት ለግብርና የተሰጠ በመሆኑ በስልጣንና ተግባሩ አንቀጽ 3 ላይ ለሆርቲካልቸር የሚሆን መሬት በጥናት ይለያል፣ከሶስተኛ ወገን ነፃ መሆኑን ያረጋግጣል የሚል ሲሆን እንዲሁም በግብርና 10 ዓመት መሪ እቅድ ገጽ 45 ከመሬት ልየታ ጀምሮ ማስተላለፍ ባለው ሂደት ግልጽነት፤ተጠያቂነትና ቅልጥፍና በተሞላበት የአከባቢን ህብረተሰብ ባሳተፈ አግባብ የአሰራር መመሪያዎች መሰረት ባደረገ መልኩ ይተገባራል የሚል በመሆኑ ሚኒስቴር መቤቱ ከሚመለከታቸው አካል ጋር በመሆን የመሬት ልየታ ተደርጎ እንዲሰጣቸው ባለማድረጉ ለአበባ እርሻ ልማት የሚውል መሬት ልየታ በተመለከተ በህገ መንግሥት እና በኢንቨስትመንት አዋጅ 1180/2012 የተሰጠው ለፌዴራል

ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ለክልል መንግስታት ነው ተብሎ የተሰጠው ምላሽ ለመቀበል የኦዲት ቡድኑ ይቸገራል፡፡

91. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብረው አለመስራቱ እና የመሬት ጥናት በማድረግ ቀጣይነት ያለውን የድጋፍና የክትትል ስራ ባለመስራቱ መሬቱ በጥናት ተለይቶ እንዳይሰጥ መሆኑ እንደምክንያት ይጠቀሳል፡፡

92. በመሆኑም ተገቢ የመሬት ልየታ ባለመኖሩ የአበባ እርሻ ድርጅቶች በሀይቅ ዳር፣በገበሬዎች መሳ መካከልና ለመኖሪያ መንደር በቅርበት መሬት በመሰጠቱ የውሃ ብክለት እንዲኖር ማድረጉ እንዲሁም በመኖሪያ አከባቢ ነዋሪዎች እርሻ አጠገብ በመሰጠቱ የአከባቢ ነዋሪ ላይ ጉዳት በማድረስ ከብቶቻቸውና ንቦቻቸውም ለሞት እየዳረጋቸው፤ በተጨማሪም አንዳንድ እርሻዎች መንገድ ዳር በመሆናቸው የከተማ ልማት ማስፋት ስራ እንዳይሰራ አድርጓል፡፡

**የአበባ እርሻ ልማቱ የሚጠቀሙትን ግብዓት መጠንና አይነት፣ አጠቃቀምና የክትትል ስርዓትን በተመለከተ፤**

93. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት የሚጠቀሙትን ግብዓት መጠንና አይነት ፣የውሀ፣ የኤሌክትሪክ ፍጆታ አጠቃቀሙን ክትትልና ግምገማ የሚያካሂድበትን ስርዓት ሊዘረጋ እና ሊከታተል ይገባል፡፡

94. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው ከታዩት የአበባ እርሻ ድርጅቶች በተገኘው ማስረጃ መሰረት፡

- አሰላ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ኤደን ሮዝ፣ ሳሮን ሮዝ አግሮፋርም ፣ ደፐሪም ቢዝነስ፣ ቲናው ቢዝነስ፣ ክላቨር፣ ብራም፣ ኦምኒ ብሎሶም፣ እና ሳታሳይ አመታዊ እርሻው የውሃ ፍጆታ መጠን፣ የግብርና ንጥረ ነገር ጥቅም ላይ የሚውል የኃይል ምንጭ እና ፍጆታውን(Input Consumption)መዝግቦ የማይዙ መሆኑ፤
- በሌላ በኩል (ጆይ ቴክ የአበባ እርሻ ድርጅት) ከከርሰ-ምድር በሞተር ጉልበት ስቦ የሚያወጣውን ውኃ ከብክነት ለመከላከል የተሰራ ሥራ የሌለ መሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምዘገባ እንዲያደርጉ የአሰራር ስርአት ዘርግቶ የድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑ፤
- በተጨማሪም ሼር ኢትዮጵያ ከሚጠቀመው የከርሰ ምድር ውሃ ያለምንም ፍቃድ እና ገደብ በሞተር ጉልበት ስቦ ( ከዝዋይ ሀይቅ) ውሃ እየተጠቀመ

ሲሆን፤ ምን ያህል ውሃ ተጠቀመ የሚለውን የማይታወቅና ከሀይቁ ለሚጠቀመው የውሃ ክፍያ የማይከፍል በመሆኑ ውሃውም እንዳይባክንና ለወደፊት ሀይቁም እንዳይደርቅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የድጋፍና ክትትል ስራ ያልሰራ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

95.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በሰጡት መልስ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል ሆኖም ክፍተቶች አይኖሩም ማለት አይቻልም ምን ያህል ያለማል ምን ያህል ግብአት ይጠቀማል የሚል ስርዓት ዘርግተን ለመስራት ጅምር ላይ እንዳለና በቀጣይ በተሻለ ለመደገፍ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

96.በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ደግሞ ይህ የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊነት እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

97.በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ የአበባ እርሻ ልማቶች የሚጠቀሟቸውን ግብዓቶች መጠንና አጠቃቀም በተመለከተ በሚ/ር መ/ቤቱ በየጊዜው በሚሰጠው የድጋፍና ክትትል አግባብ እየተሰራ ያለ ሲሆን የውሃና የኤሌክትሪኩን አጠቃቀም በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት እንዳልሆነ ግንዛቤ መወሰድ እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

98.የሚኒስቴር የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መቤቱ ባውጣው በአከባቢያዊ እና ማህበራዊ የስነ ምግባር ደንብ መሰረት በገፅ ቁጥር 78/68 የውሀ፣ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች፣ ማዳበሪያዎችና የሀይል አጠቃቀም ክትትል እና ግምገማ የሚካሄድበት ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት የተቀመጠ በመሆኑ የግብዓቶች መጠንና አጠቃቀም በተመለከተ ብቻ ድጋፍና ክትትል እንደሚደርጉና የውሃና የሀይል አጠቃቀም በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት አይደለም ብለው የገለጹ ቢሆንም ሁሉም ላይ የክትትል ስራ በመስራት ለሚመለከተው አካል እርምጃ እንዲወስዱ ማሳወቅ ያለበት በመሆኑ የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊነት አይደለም ተብሎ የተሰጠው ምላሽ አግባብነት የለውም፡፡

99. የአበባ ዘርፉን የሚመሩት የበላይ የስራ ሀላፊዎች የአበባ እርሻ ልማት የሚጠቀሙትን ግብዓት አጠቃቀም ምዝገባ አካሂደው እንዲሰሩ በዕቅዳቸው ውስጥ አካተው እስከ ታችኛው ፈጻሚ አካል ድረስ በማውረድ የክትትል ስርአቱን ዘርግቶ ባለመከታተሉ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

100. በመሆኑም ሚኒስቴር መቤቱ የአበባ እርሻዎች የውሃ ፍጆታ መጠን፣የግብርና ግብዓቶች/ፀረ አረም፣ፀረ ተባይ/ ፀረ ፈንገስ እና ማዳበሪያ አጠቃቀሙን፣ ጥቅም ላይ የሚውል የኃይል ምንጭ እና ፍጆታውን መዝግቦ ባለመያዙ በአመት ምን ያክል ለማምረት እንደሚጠቀሙ ስለማይታወቅ ድርጅቶቹ ለማምረት የሚጠቀሙትን ግብአቶች ከልክ በላይ በማስገባት ሀገሪቷ ማውጣት የሌለባትን የውጪ ምንዛሬ እንድታወጣ ያደርጋታል፤ እንዲሁም በሞተር ጉልበት ስቦ ከሀይቅ/ከጉድጎድ የሚጠቁሙት ውሃ ክፍያ የማይከፍሉበት በመሆኑ ለወደፊት በሀይቁ ላይ የውሃ የመቀነስና የምንጭ መድረቅ ሊያስከትል ይችላል፡፡

**የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ በተመለከተ፤**

101. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ስራ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ቀርፆ ተግባራዊነቱን እና ውጤታማነታቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

102. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩት ባለድርሻ አካላት እንዲሁም የአበባ እርሻ ድርጅቶች ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማቱን ሲያለሙ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ቀርጸው ተግባራዊ እንዲደረግ የተደረገ ድጋፍና ክትትል የሌለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

103. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ ፤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ በተናጠል የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች ላይ የአፈርና ውሃ ጠብቀው እንዲሰሩ ተቀርፆ የተተገበረ ፕሮግራምና ፕሮጀክት የለም፤ ነገር ግን ለወደፊት የሚሰራ መሆኑን እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ ጊዜያት በዘርፉ ለተሰማሩ የአበባ ኩባንያዎች በአፈር እና ውሃ አያያዝና አጠቃቀም፣ የውሃ ተፋሰስና እርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እንደሰሩ ገልጸዋል፡፡

104. የሚኒስቴር የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ለአበባ እርሻ ድርጅቶች የተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች የሰጠበትን ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ስላልቀረበ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ይቸግራል፡፡

105. በሚ/ር መ/ቤቱ የተፈጥሮ ሀብት ዳይሬክትሬት የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶችን ቀርፆ እየሰራ ያለ ቢሆንም፤ ለሀገሪቱ ከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ እያስገኙ እና በከፍተኛ ሁኔታ አፈርና ውሃ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የአበባ እርሻ ድርጅቶችን ላይ ትኩረት ሰጥቶ እና በእቅዱ አካቶ አለመስራቱ ለዘርፉ ትኩረት አለመስጠት እንደምክንያት ይሆናል፡፡

106. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ስራዎችን የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ቀርፆ ተግባራዊነቱን እና ውጤታማነታቸውን ባለመከታተሉ በአፈር እና በውሃ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተፅዕኖ በማወቅ ቅድመ ጥንቃቄ እንዳይደረግና የደረሰውንም ጉዳት ታወቀ የእርምት እርምጃ እንዳይወሰድ ያደርገዋል፡፡

**የመልካም እርሻ አተገባበር ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን በተለመከተ፤**

107. ሚ/ር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለዉ የመልካም እርሻ አተገባበር ሥርዓት በሁሉም የአመራረት ሥርዓቶች ተግባራዊ መሆኑን ሊደግፍና ሊከታተል ይገባል፡፡

108. በግብርና ሚኒስቴር የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ የመልካም እርሻ አተገባበር ስርዓትን ከማስፋን አኳያ ከምርምር የሚወጡ ቴክኖሎጂ የመረጃ አቅርቦትን መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ መሆኑን ይገልጻል፡፡

109. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለዉ የመልካም እርሻ አተገባበር ሥርዓት (ዘላቂ የአካባቢ ልማት፣ የሰራተኛ መብት እና የስራ ቦታ ደህንነትና ጤንነት ጠብቀው ከአአባቢ ማህበረሰብ ተስማምተው) ተከትለው ምርትና ምርታማነቱን እንዲጨምር የአመራረት ሥርዓቶች ተግባራዊ እንዲያደርጉ በጥራት ቁጥጥርና ክትትል ላይ የተመሰረተ የአመራረት ሰርቲፊኬሽን ሥርዓት ባለመኖሩ በገበያ ላይ ክፍተት መፍጠሩ፡፡

110. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአለም አቀፍ ገበያ የሚጠይቃቸው የመልካም እርሻ አተገባበር (GAP-Good Agricultural Practices) ገበያው በሚፈልጋቸው መንገድ መስራት አልቻለም፣

111. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በሰጡት ምላሽ የስራ ላይ ደህንነት ተጠብቆ እንዲሰሩ ከሰሩት ስራ ለአብነት አፍሪ ፍላወር ( ሆለታ)

ኬሚካሉ መረጨት በሌለበት ሰዓት ተረጭቶ ሰራተኛው ጉዳት ደርሶበት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ እንዳደረጉና የአበባ እርሻ ኢንቨስትመንት ስራው የግብርና ሚኒስቴር ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ብዙ ስክተሮች ሀላፊነት ስለሆነ ሁሉም አካላት መጠየቅ ቢቻል ጥሩ ነው ብሏል፡፡

112. በነባራዊ ሁኔታ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ እርሻዎቹ ዘላቂ የአካባቢ ልማት፣የሰራተኛን መብት እና የስራ ቦታ ደህንነትና ጤንነት (OHS) ጠብቀው ስራቸውን እንዲያከነውኑ የሰራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ሊጎዱ የሚችሉ ሁኔታዎች ስለመኖሩ እና በስራ ሁኔታቸው ለጤና መታወክ ተጋላጭ የሆኑ ሰራተኞች መደበኛ የጤና ምርመራ ጊዜ ስለመኖሩና የመፍትሄ እርምጃዎች ስለመወሰዳቸው በተለይ ቀደም ሲል የሆርቲካልቸር ኤጀንሲና የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን በነበሩበት ወቅት የድጋፍና ክትትል ስራ ሲሰራ ነበር ግን በተደጋጋሚ ጊዜ በተለያየ መዋቅር በመደራጀቱ የተጠናከረ ድጋፍ ለመስጠት የአደረጃጀት ችግር የነበረ በመሆኑ ስራው በሚፈልገው ደረጃ እንዳልተከናወነ ገልጸዋል፡፡

113. ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ቀጣይነት ባላው የዘርፉ እድገት እና ከአከባቢው፣ ከማህበረሰቡ፣ ከሰራተኛው እንዲሁም ከተፈጥሮ ሀብቱ ጋር እንዴት አጣጥሞ በማስኬድ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚቻል ዘርፉን የሚመለከተው አካል ወጥ የሆነ ስራ አለመስራት እንደ ምክንያት ይጠቀሳል።

114. በመሆኑም የመልካም እርሻ አተገባበርን አሟልተው ባለመስራታቸው የሚጠቀሙት ግብአት በአግባቡ ስለማይዙና ስለማያስወገዱ በአከባቢ ያለውን ንፁህ ውሃ እንዲበከልና በአከባቢ የሚደርሰውን ጉዳት ለመከላከል እንዲያስቸግር አድርጓል፡፡

**የፀረ-ተባይ ኬሚካል ግብዓቶች ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱን ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ**

115. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች የሚጠቀሙት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ግብዓቶች ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

116. የፀረ- ተባይ ምዝባና ቁጥጥር አዋጅ 674/2002 ክፍል ሦስት አንቀፅ 17 የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች የሚጠቀሙት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ግብዓቶች ተመዝግቦ ወደ

ሀገር ውስጥ መግባታቸውን መከታተልና መቆጣጠር እንዳለበት ሀላፊነት ለግብርና ሚኒስቴር ተሰቶታል ፡፡

117. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣

- የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች የሚጠቀሙት የፀረ-ተባይ ኬሚካል ግብዓቶች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ ሳይመዘገቡ የሚገቡ እንደሆነና በጉምሩክ በኩል ሲገባም የፍቃድ ወረቀት ከመስጠት ውጪ ያስገቡት ግብአት ከምን ያክል ቆይታ በኋላ አገልግሎት አይሰጥም የሚለውና ያስገቡት ግብአት ስለትክክለኛነቱ ቦታው ድረስ ሄዶ እንደማያረጋግጡና ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባም ያልተከታተለና ያልተቆጣጠረው መሆኑ፤
- በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአግሮ ኬሚካሎች መጠን ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲገዛና እንዲሰራጭ፣ በግልጸኝነት ላይ የተመሰረተ የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ተገቢውን ክትትል ያላደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

118. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ የሚገቡት ግብአት በሙሉ ተመዝግበውና ፍቃድ አግኝተው የሚገቡ ሲሆን ከፍቃድ ውጪ ካስገቡ እርምጃ እንደሚወሰድና የአበባ እርሻ የሚጠቀሙት ኬሚካሎች በየጊዜው ስለሚለያይ ሳይመዘገብ የሚገባ እንደሆነ እና ለሚ/ር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆነ የግብርና ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 509/2022 በአዲስ መልክ በቅርቡ የተቋቋመ በመሆኑ ይህ ተግባር ቀደም ሲልም ጅምር ስራዎች ያሉት ቢሆንም በተጠናከረ መልኩ ወደፊት እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

119. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሰጠው ሀላፊነትና ስልጣን መሰረት የአበባ ዘርፉን የሚመሩት የበላይ ኃላፊዎችም ሆኑ ፈፃሚዎች የአበባ እርሻ ድርጅቶች የሚያስገቡትን ግብአት ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ግብአቱን በቦታው ድረስ ሄዶ አረጋግጦ፤ እንዲገባ የክትትል ስርዓት ዘርግቶ አለመከታተሉ እንደ ምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡

120. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች የሚጠቀሙት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ባለማድረጉ ድርጅቶቹ ለእርሻቸው ከሚፈልጉት በላይ በማስገባት ሀገሪቱ መቅረት የነበረበት የውጪ ምንዛሬ ተጨማሪ እንዲወጣ ከማድረጉም በላይ፤ ፀረ-ተባይ ኬሚካሉ በአበባ እርሻ ድርጅቱ

ውስጥ ተከማችቶ እንዲገኝ ያደርጋል እንዲሁም ለህገ ወጥ የፀረ ተባይ ኬሚካል ንግድ በር እንዲከፈት ያደርጋል፡፡

**የአበባ አልሚ ድርጅቶች የማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ እና የአከባቢ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀታቸውን በተመለከተ**

121. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማቱ ሊኖረው የሚችለውን ተፅዕኖ ለመለየትና ለመገምገም የሚረዳ የአከባቢ ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ስለማዘጋጀታቸው (ESIA) እና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ (Environmental management plan) ተግባራዊ ማድረጋቸውን በክልልና በሚመለከታቸው አካላት ስለመገምገሙ ሊከታተል ይገባል።

122. ይሁን እንጂ ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠ በታዩት፤

- በስምንት የአበባ እርሻ ድርጅቶች (አሮው ኤክስፖርት ፤ኤደን ሮዝ፣ ሳሮን ሮዝ አግሮፋርም፣ ደፕሪም ቢዝነስ፣ ቲናው ቢዝነስ፣ አቢሲኒያ ፍላወር ሀ/የተ/የግ/ማህበር፣ ኦምኒ እና ክላቨር የአካባቢ ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ (ESIA) ሳያዘገጁ ወደ ስራ የገቡ ሲሆን፤ አሰላ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ሳታሳይ ፋርም፣ ዲፕሪም ፋርም ፤ኦምኒ ብሎሶም እና ክላቨርሃ/የ/የግ/ማህበር የአከባቢ አያያዝ ዕቅድ (Environmental management plan-EMP) ማዘጋጀት ሲገባቸው ያላዘጋጁ ሲሆን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱም የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች የማህበራዊና የአከባቢ አያያዝ ዕቅድ (EMP) አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲደያርጉ ክትትል በማድረግ በሚመለከታቸው አካላት እንዲገመገም ክትትል ያደረገበት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በተጨማሪም ሼር ኢትዮጵያ፣ አሰላ ፍላወር፣ እና ጆይቴክ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የአከባቢ ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ (ESIA) የአባባ ልማት ስራውን ከመጀመራቸው በፊት ማዘጋጀት ሲገባቸው ስራውን ከጀመሩ በኃላ ያዘጋጁ መሆናቸው፡
- በሌላ በኩል በወጣው የአከባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 ማንኛውም ፕሮጀክት ኢንቨስትመንት ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊት የአካባቢ ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ (ESIA) እንዲያዘጋጁ የሚል አስገዳጅ አዋጅ የወጣ ሲሆን፤ ሁሉም የአበባ እርሻ ድርጅቶች ከ1996 በኃላ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ

ቢሆንም፤ የአከባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ሳያዘጋጁ ወደ ስራ የገቡ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ማወቅ ተችሏል፡፡

123. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በሰጡት መልስ የአበባ እርሻ ድርጅቶች ጥናቱን አዘጋጅተው እንዲያስገመግሙ በቅንጅት መስራት ያለብን ቢሆንም አልሰራንም ምክንያቱም በዋናነት የኛ ሀላፊነት ሳይሆን የአከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እንደሆነና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚሰራቸው ስራዎች እና ፕሮጀክቶች የአካባቢ ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ አዘጋጅተው በአከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አፀድቀው እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

124. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ ተግባሩ የፌደራል እና የክልል አካባቢ ጥበቃ ተቋማት ሲሆን በሚ/ር መ/ቤቱ ቀደም ሲል የነበረዉ የግብርና ዘርፍ አካባቢ ጥበቃ መዋቅር እንዲፈርስ በመደረጉ ተቀናጅቶ ለመስራት አስቸጋሪ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በወቅቱ በነበረው አሰራር መሰረት መሬት የተረከቡ በመኖራቸው ምክንያት ሰነዶቹን ሳያዘጋጁ ወደ ስራ የገቡ እርሻዎች ስላሉና የአካባቢና ማህበራዊ አያያዝ ዕቅድ (Environmental and social management plan) ሰነድ ማዘጋጀት ስላለባቸው ይህንን ለወደፊቱ ለማስተካከል ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር ተቀናጅተው እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

125. የኢቨስትመንት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በመሆን በቅንጅት ለማስራት ያለው ሁኔታ ደካማ በመሆኑ እንዲሁም በአዲሱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ መዋቅር የግብርና ዘርፍ አካባቢ ጥበቃ መዋቅር እንዲፈርስ በመደረጉ የሌላ አካል ሀላፊነት ነው ብሎ መታሰቡ እንደ ምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡

126. በመሆኑም የአበባ እርሻ ድርጅቶች የአከባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቱን ባለመሰራቱ የፕሮጀክቱና ልማት ተፅዕኖዎችን ስለማይተነበይና ስለማይገመገም፤ የህብረተሰቡን አሰራር ለውጦችን(የህይወት ዘይቤና እሴቶችን) እንዳይታወቅ ስለሚያደርግ በሰውና በአከባቢ ደህንነት ላይ ስጋት ከመፍጠሩ በላይ በአጠቃላይ ስርዓተ ምህዳሩ (ECOSYSTEM) ላይ የሚያስከተለው አሉታዊ ተጽዕኖ በመከታተልና በመቆጣጠር እንዲሁም የተጠያቂነት ስርዓት እንዳይኖር ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

**የአበባ አልሚ ድርጅቶች የተቀናጀ ተባይ መከላከል /IPM/ እንዲተገበሩ ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ**

127. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች አካባቢን ከመጠበቅ አንፃር የተቀናጀ ተባይ መከላከል /IPM/ እንዲተገበር ሊደግፍና ሊከታተል ይገባል፡፡

128. ይሁን እንጂ ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተገኘ መረጃ የኬሚካል አጠቃቀም እንዲቀንስና የተቀናጀ የተባይ መከላከያ(IPM) እንዲተገበር፤ በ(IPM) ትግበራ ጥሩ ልምድ ካላቸው ጋር ግንኙነት በማድረግ ስልጠና መሰጠቱና ከኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ጋር በመሆን እራሱን የቻለ ፖሊሲ እንዲወጣ የላከ እንደሆነ በአምስት የአበባ እርሻ ድርጅቶች ላይ (በሼር ኢትዮጵያ፣በራም፣ሀርበርግ፣ኤኬው ሮዝ እና በዝዋይ ሮዝ) ተግባራዊ እንዲያደርጉ እየሰሩ ቢሆንም፤ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በአምስቱም የተጠቀሱት የአበባ እርሻ ድርጅቶች በትክክል ተግባራዊ አድርገው እየሰሩ ስለመሆናቸው እና ሌሎችም የአበባ እርሻ ድርጅቶች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ምንም አይነት ድጋፍም ሆነ ክትትል እንዳላደረገላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

129. በሌላ በኩል በሆርቲካልቸር ዘርፍ የኤክስፖርት ልማት ድጋፍ ክትትልና ፋሲሊቴሽን ዳይሬክቶሬት ዕቅድ በ2013 በጀት አመት ዕቅድ (የብቃት ማረጋገጫ፣ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ/IPM/ የህግ ማዕቀፍ እና የአሰራር ስርዓቶች) ባለቤት ተፈጥሮላቸው ደረጃ በደረጃ እንደሚተገበር ታሳቢ አድርጎ ለመስራት ያቀደ ቢሆንም ባቀደው መሰረት ያላከናወነ መሆኑ፤

130. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ- መጠይቅ፣ በሰጡት መልስ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ/IPM/ እንዲጠቀሙ እንደሰሩና፤ 50% የሚሆኑ Biological IPM (ተፈጥሮአዊ የተቀናጀ የተባይ መከላከያ) እንዲጠቀሙ የባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እንዳደረጉና እርሻ ድረስ ሄደው ክትትል እንደማያደርጉ እና Biological IPM (ተባዩ) ውሃ ላይ እና አከባቢ ላይ እንዳይለቀቅ እየሰሩ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

131. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠው ምላሽ ለሚ/ር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆነ የግብርና ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 509/2022 በአዲስ መልክ በቅርቡ የተቋቋመ በመሆኑ ይህ ተግባር ቀደም ሲልም ጅምር ስራዎች ያሉት ቢሆንም በተጠናከረ መልኩ ለወደ ፊት ይሰራል ብለዋል።

132. በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምልሽ ይህ ቀደም ሲል የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በነበረበት ወቅት በቂ ልምድ የሀገር ዉስጥ እና የውጭ ተሞክሮ ተወስዶ ሲሰራበት የቆየ የነበረ ቢሆንም አደረጃጀቱ በተደጋጋሚ በመቀያየሩ በሚፈለገው አግባብ ማስኬድ እንዳልተቻለ ግንዛቤ ቢወሰድ በቀጣይ በእቅድ ተይዞ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

133. የአበባ ዘርፉን የሚመሩት የባላይ የስራ ሀላፊዎች የተቀናጀ የተባይ መከላከያ(IPM) አስፈለጊነት ቢረዱም ለማስተግበር አትኩሮት ሰጥቶ እንዲተገበር የትግበራውን ስርአት ባለመዘርጋቱና እንዲተገበርም የድጋፍና የክትትል ስራ አለመስራቱ አንዱ ምክንያት ነው፡፡

134. በመሆኑም የተቀናጀ የተባይ መከላከያ /IPM/ ተግባራዊ ባለማድረጉ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን ኬሚካል በመቀነስ፤ ሀገሪቷ ለኬሚካሉ የሚታወጣውን የውጪ ምንዛሪ እንዳይወጣና ኬሚካሉ በሰራተኛም ሆነ በአከባቢው ማህበረሰብ የሚደርሰውን ጉዳት እንዳይቀንስ ያደርገዋል፡፡

**በአበባ ልማት ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች የሰብአዊ መብቶች፣ የስራ አከባቢ የደህንነትን በተመለከተ፡**

135. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከተቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአበባ እርሻ ድርጅቶች ሀገራዊና እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች፣ የስራ አከባቢ ምቾትን ከስራ ጋር ተዛማች የሆኑ ስልጠናዎች፤ የደህንነት መጠበቂያ ቁሶች ፤የጤና ምርመራ ድንጋጌዎች መሰረት  የሰራተኛን የሰብኣዊ መብት መከበሩን ስርዓት ዘርግቶ ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

136. ይሁን እንጂ ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተሰበሰበ መረጃ መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የሚጠቀሙት የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአለም ጤና ድርጅት የተፈቀደና የኬሚካሎቹ መግለጫ እና የአደጋ ማስጠንቀቂያ ምልክቶች አጠቃቀምን በሚገልፅ መልኩ እንዲቀመጥ የክትትል ስርአት ዘርግቶ ክትትል ያደረገበት ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ለአብነትም ፡-

- በ6 የአበባ እርሻ ድርጅቶች (ድሬ ባይ ኮላር፣ አቢስኒያ፣ ዲፕሪም፣ ሳታሳይ፣ ኦምኒ፣ እና ቤቲ ኦርናሚንታል) የአበባ እርሻ ግሪን ሀዉስ መግቢያዉ በር ላይ የተባይ መከላከያ ኬሚካል መቹ እንደተረጨ፣ ወደ

ዉስጥ መግባት የሚቻለዉ ከምን ያህል ሰዓታት ቆይታ በኋላ እንደሆነ፣ የተረጨዉ የኬሚካል ዓይነት… የመሳሰሉት መረጃዎች በሚገልፅ መልኩ ያልተቀመጠ መሆኑ እና ሰራተኞቹ ምንም አይነት የአፍም ማስክና የእጅ ጓንት ሳያደርጉ ስራቸውን እየሰሩ መሆኑ፤

- በ5ቱ (ሳታሳይ፣ ኤደን ሮዝ፣ ለዲኘሪም፣ ቤቲ ፋርም፣ድሬ ባይ ኮላር) ምንም አይነት ስልጠና ለሰራተኞቸው እንዳልሰጠና የሕክምና መስጫ ክሊኒክም (clinic ) ሆነም ስልጠና የሚሰጥ ነርስ የሌለውና ሰራተኞች የስራ ላይ ደህንነት/ ሴፍቲ/ የማይጠቀሙና በኬሚካል ርጭት ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች ስታንዳርዱ ዝቅተኛ የሆነ የስራ ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች /PPE/ የሚጠቀሙ መሆኑ፤ ፍሳሽ ማስወገጃና ማጠራቀሚያ ስለሌለው በክረምት ወቅት ወደ አካባቢ ፍሳሹ ስለሚለቀቅ፤ በተጠራቀመው ውሃ በወባና ታይፈስ በሽታ ሠራተኞች እየተያዙ መሆኑ፤ በሥራ ቦታ ራሱን የቻለና ደረጃውን የጠበቀ የሕክምና አገልግሎት መስጫም ሆነ ታካሚ የሚያጓጉዝ መኪና የሌለው መሆኑ፤
- ሳታሳይ የኬሚካል ጉዳት ደረጃው ሰማያዊ (Class 3) እና አረንጓዴ (Class 4) ኬሚካል እንደሚረጩና ለሚረጩትም ሰራተኞች በየወቅቱ የጤና ምርመራ እንደማያደርግ፤ ማረፊያ ቦታ ገና ያልተገነባላቸው መሆኑ፣ ሠራተኞች ኬሚካል ሲረጩ የሚለብሱት ቦቲ (ጫማ) ያልተሟላላቸው መሆኑ፤
- አቢሲኒያ ፍላወር ለሰራተኞ በገባው ውል መሰረት ተመጣጣኝ የስራ ክፍፍል የማይሰጣቸውና(ከልክ በላይ ስራ መስጠት) እንዲሁም የስራ ላይ ደህንነት መከለከያ ትጥቅ ቁሳቁሶች(PPE)ለአንዳንዶቹ ኬሚካል ስለሌለው በሚል ሰበብ የማያሟላ ሲሆን፤ በሰራተኞቹ ላይ የቆዳ አላርጂክ ፣የፊት ማሳከክ፤ ፊታቸው ላይ ነጫጭ እንዲሁም ብዙ ጊዜ ቆመው ስለሚሰሩ የጀርባ ሕመም መከሰት፤ ኬሚካል ለሚረጩትም ቅያሪ የሚሆን ተጨማሪ የሆነ ትጥቅ የሌለና እንዲገዛላቸው ቢጠየቁም እንዳልተገዛላቸውና የጤና ኢንሹራንስ ያልተገባለቸው መሆኑ፤




ፎቶ-5 አቢሲኒያ ፍላወር ራስን መከለከያ ትጥቅ ቁሳቁሶች(PPE) አለመጠቀም

- በተጨማሪም ጂቱ ሆርቲካልቸር ለሰራተኛ የስራ ላይ ራስን መከለከያ ትጥቅ ቁሳቁሶች(PPE) ያላሟላና ምግብ የሚመገቡበትና ልብስ የሚቀይሩበት ቦታ፡ ሽንት ቤት ፡ የመታጠቢያ ቤት የሌለው መሆኑ፤

137. በተጨማሪም ከባለድርሻ አካላት ከተሰበሰበ ማስረጃ ለአብነትም፡-

- ደቡብ ም/ሸዋዞን ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ በሰጡት ምላሽ (አሰላ ፍላወር) የደህንነት ቁሳቁሶች/PPE/ ባለመሟላቱ በኬሚካል መመረዝ የሚደርስ የቆዳ አላርጂክ ጉዳቶች እንዳለና በሠራተኞች ፌዴሬሽንም መጥተው የሰራተኛ ማህበር እንዲያቋቋም የተነገረው ቢሆንም፤ እስከ አሁን በድርጅቱ የሰራተኛ ማህበር የሌለው መሆኑ፤
- ደቡብ ምዕራብ /ሸዋ ዞን አከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ክትትል ሲደረግ በድርጅቱ ለሠራተኞችም ሆነ ለባለሙያዎች ስልጠና ስላልተሰጠ የእውቀትም ሆነ የግንዛቤ ችግር ስላለ (በአሰላ ፍላወር) ሰባት ሰው ከባድ ጉዳት ደረሰባቸው አዲስ አበባ ሆስፒታል ክትትል ላይ ያሉ ሲሆን፤ ሠራተኞቹም ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው መስራት ላይ ክፍተት ያለበት መሆኑ፤
- በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ አከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአበባ አልሚ ድርጅቶች ውስጥ

የሚሰሩ ሰራተኞች እስታንዳርዱን ያልጠበቀ የስራ ላይ ደሕንነት መከላከያ እንደሚጠቀሙና ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ አብዛኛው የአበባ እርሻ እያንዳንዱ ክፍል ካሜራ ስላለ ትክክለኛውን መረጃ ሲሰጡ ከስራ እንደሚባረሩና የድርጅቶቹ ባለሀብቶች ወደ ኢንቨስትመንቱ ሲጋበዙ ርካሽ የሰው ሀብት አለ ተብለው ስለሆነ፣ ጉልበት ብዝበዛ እንደያሚካሂዱና የሠራተኞች ማህበር በጥሩ ሁኔታ ባለመደራጀቱ የሰራተኞች መብቶችና ደህንነት በሚገባ እየተጠበቀ እንዳልሆነ መገለጹ፤

138. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፡ በዋናነት ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች የሚመለከት ሲሆን አብዛኛዎቹ ሰራተኞች ቅሬታቸው ዝቅተኛ ደሞዝ ስለሚከፈላቸው እንደሀገር ዝቅተኛ ክፍያ ጣሪያ ባለመኖሩ ይህንን ቅሬታ ለመፍታት መሞከሩን ገልጸዋል፡፡

139. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ይህን የመቆጣጠር ተግባር እና ኃላፊነት የፌዴራል እና ክልል የአካባቢ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን/ቢሮ ሲሆን ግንዛቤ የመስጠት ስራ ግን በተደጋጋሚ በሚ/ር መ/ቤቱ ባለሞያዎች ሲሰጥ እንደነበር ገልፀዋል፡፡

140. በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምልሽ ይህን የመቆጣጠር ተግባር እና ኃላፊነት የክልል እና ፌዴራል ስራና ክህሎት ሚ/ር/ቢሮ (የቀድሞ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር) እና የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ሲሆን ቅንጅት ሲፈልጉ አስፈላጊዉ ድጋፍ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

141. የበላይ የስራ ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ የአበባ እርሻ ድርጅቶች ምርታቸውን ሲያመርቱ ለሰራተኛው መሟላት ያለበት ቁሳቁስ አሟልተው እያሰሩ መሆናቸውን የድጋፍና የክትትል ስራ መስራት እንዳለበት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው የኢትዮጵያ ሃላፊነት የተሞላ ኢንቨስትመንት እውን ለማድርግ የሚያስችል የአከባቢያዊ እና ማህበራዊ የስነ ምግባር ደንብ ውስጥ ለሰራተኞች የሰብአዊ መብቶች መጠበቁን፣ የስራ አካባቢ ምቹትን ከስራ ጋር ተዛማች የሆኑ ስልጠናዎች፤ የደህንነት መጠበቂያ ቁሶች ፤የጤና ምርመራ ድንጋጌዎች መሰረት የሰራተኛን ሰብኣዊ መብት መከበሩን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ መከታተል የተሰጠው ተግባር ሲሆን የሰራተኞች መብትና ደህንነት የመጠበቅ ሃላፊነት የተሰጠው ስልጣንን ተግባር ጉዳዩ ለሁሉም

መ/ቤቶች ይሰሩበት ዘንድ የተሰጠ አካታችነት/ዘርፈ-ብዙ ያለው ስለሆነ የተሰጠው መልስ ተቀባይነት የለውም፡፡

142. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጣው የአሰራር ስነ ምግባር ደንብ መሰረት ስራቸውን መፈጸማቸውን ጠንካራ የድጋፍና የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ባለመከታተሉና ከሚመከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ያሉት ችግሮች እንዲፈቱ አለማድረጉ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

143. በመሆኑም የሰራተኞቹን ደኅንነትና ጤንነት በሚገባ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን እንዲወስዱ የሚረጋገጥበት ስርዓት ዘርግቶ በአግባቡ ባለመስራቱ የሰራተኞችን ደኅንነትና ጤንነት ለመጠበቅ መሟላት ያለበት የደህንነት መሳሪያዎች ሳይሟላ እንዲሰሩ ስለሚገደዱ ድርጅቱ ምርቱን ለማምረት የሚጠቀመው ግብአት በሰራተኛው እስከሞት ሊያደርስ የሚችል የተለያየ የጤና ጉዳት እያደረሰ የሚገኝ ሲሆን፤በአንዳንድ ድርጅቶች ለሰራተኛው የጤና ምርመራ ስለማይደረግላቸው ስለ ጤናቸው ምንም እንዳያውቁ አድርጓል፡፡

**በአበባ አልሚ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ሴት ሠራተኞች ጤንነታቸውና እና የስራ ቦታ ደህንነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸው መጠበቁን በተመለከተ፡**

144. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ እርሻ ድርጅቶች የሚሰሩ ሴት ሠራተኞች ጤንነታቸው እና የስራ ቦታ ደህንነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸው ተጠብቆ እየሰሩ ስለመሆናቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

145. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሴቶች በአበባ እርሻ ልማት አሁን ባለው አሰራር በሴቶች ላይ የሚደርሱ ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ ያለማግኘታቸው እና የሥራ ዋስትና ማጣት ማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች ከፍተኛ መሆኑ እንዲሁም ሴቶችና ወጣቶችን በዘርፉ በባለሀብትነት ለማሰማራትና ተጠቃሚ ለማድረግ የተሰሩ ሥራዎች ውስን በመሆኑ የተሻሻለ አሰራርን ቀርጾ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ማወቅ ተችሏል፡፡ ለአብነትም፡-

- ኦምኒ ብሎሶም ሴቶች በኬሚካል መቀመም ስራ ላይ ተሰማርተው የሚሰሩ መሆኑ ለሰራተኛው የሚያስፈልገው መሰረታዊ የስራ ላይ ራስን መከለከያ ትጥቅ ቁሳቁሶች (PPE) እና የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ

ማዕከል እንዲሁም ከስራ ጋር ተዛማች የሆኑ ስልጠናዎችን ያልሰጠ መሆኑ፤

- የአብሲኒያ ፍላወር ኃ/የ/የግ/ማ ለሴት ሰራተኞች ተብሎ ለብቻ የሚደረግ ምርመራና ጥበቃ እንደሌለው ሰራተኞች ሁሉም የሚሰሩትን ስራ እንደሚሰሩና ቀዝቃዛ ክፍል ላይ ለሚሰሩት ሰራተኞች ቀደም ሲል ሻይ እንደሚጠጡና በአሁን ሰዓት ይህም የቀረ መሆኑ እና አበባ የሚቆርጡትም ረጅም ሰዓት ቆመው በመሆኑ ለኩላሊት በሽታ መጋለጣቸው፣ እንዲሁም አበባው ከመስክ ተቆርጦ ሲመጣ የሚታጠብበት ሊፍ ሻይን(leaf shine spray) የሚባለውን ቀላቅሎ የሚያጥቡ ሲሆን፤ ምንም አይነት ጓንት የማይጠቀሙ መሆኑ፤
- ኤደን ሮዝ ለሴት ሰራተኞች ምንም አይነት የስራ ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ ሳያሟላ እና የስራ ቦታ ደህንነታቸው ጤንነታቸውን እየተጠበቀ ስራቸውን የማይሰሩ በየወቅቱ የጤና ምርመራ የማይደረግላቸው መሆኑን፤



ፎቶ-6 ኤደን ሮዝ የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ አለመኖር የሚያሳይ

146. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በሰጡት መልስ በየስድስት ወር ሴት ሰራተኞች የደም ምርመራ እንዲያደርጉ እንደሚደረግና ማህበሩ ከአበባ እርሻዎቹ ጋር በመሆን የጾታ (gender department) እየሰሩ ቢሆንም

እንደ ግብርና ሚኒስቴር እዚህ ላይ አልሰራንም በቀጣይ የሴቶች ዳይሬክቶሬት ጋር በመቀናጀት በቼክ ሊስት ውስጥ አስገብተን ለወደፊት የሚሰራ መሆኑን ግልጸዋል፡፡

147. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፤በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት መልስ ይህን የመቆጣጠር ተግባር እና ኃላፊነት የክልል እና ስራና ክህሎት ሚ/ር (የቀድሞ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር) እና ሴቶች ጉዳይ ሚ/ር ሲሆን ቅንጅት ሲፈልጉ አስፈላጊዉ ድጋፍ ይደረጋል ብሏል፡፡

148. የበላይ የስራ ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ የአበባ እርሻ ድርጅቱ ውስጥ የሚበዙት ሴቶች እንደ መሆናቸው የአበባ እርሻ ድርጅቶች ምርታቸውን ሲያመርቱ ለሰራተኛው መሟላት ያለበት ቁሳቁስ አሟልተው እያሰሩ መሆናቸውን የድጋፍና የክትትል ስራ መስራት እንዳለበት ባወጣው የአካባቢያዊ እና ማህበራዊ የስነ ምግባር ደንብ የተቀመጠ ሲሆን፤ እንዲሁም በሚ/ር መ/ቤቱ የሴቶችን ዳይሩክቶሬት በመኖሩ የአበባ ዘርፍ ከሚመሩት ዳይሬክተር ጋር ተቀናጅቶ በመስራት የሚፈለገው ቁሳቁስ ተሟልቶላቸው እየሰሩ መሆኑን የክትትል ስርአት ዘርግቶ ባለመስራቱ የተሰጠው ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

149. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአባባ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ሴት ሠራተኞች በህጉ መሰረት መስራት ያለባቸውን እና ማግኘት ያለባቸውን ጥቅም በማስመልከት የክትትል ስራ አለመስራቱ እንደ ምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡

150. ስለሆነም መሟላት ያለበት የስራ ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ ባለመሟላቱ እንዲሁም ለሴቶች ተገቢ ባልሆነ የስራ መደብ ላይ (በኬሚካል መቀላቀያ ክፍል) በማሰራት ለውርጃ፣ተፈጥሮዉን ያልጠበቀ ልጅ መውለድ አደጋዎች እንዲከሰት ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የቆሻሻ አያያዝና እና አወጋገድ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡**

151. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአበባ እርሻ ድርጅቶቹ የሚወጡ ቆሻሻዎች በሚመከማችበት፣ በሚጓጓዝበት፣ በሚወገድበት፣ ስርዓት መዘርጋቱንና በሰዎችና በእንስሳት ጤና እና በአከባቢ ብክለት በማያስከትል መልኩ ቆሻሻ በአግባቡ መያዙንና መወገዱን ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

152. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው ከታዩት የአበባ እርሻ ድርጅቶች ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአበባ እርሻ ድርጅቶቹ የሚወጡ ቆሻሻዎች በሚከማችበት፣ በሚጓጓዝበት፣ በሚወገድበት፣ ስርዓት መዘርጋቱንና በሰዎችና በእንስሳት ጤና እና በአከባቢ ብክለት

በሚያስከትል መልኩ ቆሻሻ በአግባቡ መያዝና መወገዱን ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ክትትል ያላደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለማሳያነት፡-

- በአምስ አበባ እርሻ ድርጅቶች (ኦምኒ ብሎሶም፣ አሰላ ፍላወር፣ ሳሮን ሮዝ፣ አግሮፋርም፣ ለአቢሲኒያ ፍላወር) የቆሻሻ አያያዝና አወጋገዱ ሲታይ የፈሳሽ ቆሻሻ ለማስወገድ የፈሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ /መከሚያ ቴክኖሎጂዎች(soak away pit) እንጠቀማለን ቢሉም ደረጃውን ያልጠበቀና የሚወጣው ፈሳሽ ቆሻሻ በአከባቢው ማህበረሰብ ላይ ችግር እያመጣ መሆኑ፤ ከፈሳሽ ቆሻሻው በተጨማሪ ጥቅም ላይ የማይውሉ ፕላስቲኮችን፤የአበባ ተረፈ ምርቶችን እዚያው ውስጥ የሚያጠራቀም ሲሆን በከርሰ ምድር ውሃ ላይ ምን ችግር ያመጣል ብለው ምርመራ የማያደርጉ መሆኑ፤
- በተጨማሪም(ኦምኒ ብሎሶም) ደረቅ ቆሻሻን ለማስወገድ ከምንጩ ተለይተው በደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎቹ ላይ የጽሁፍ/ምልክት የማይፃፍበት እና ቆሻሻው የሚቃጠልበት ደረቅ ቆሻሻው የተለየ ቴክኖሎጂ (incinerate) የሌለውና ቆሻሻው ግቢ ውስጥ ተጠራቅሞ ያለ መሆኑ፤



**ፎቶ-7 በማከሚያ ቴክኖሎጂዎች (soak away pit) ውስጥ (ፕላስቲክ፣ ተረፈ ምርት፣ ፈሳሽ ቆሻሻ አንድ ላይ የሚጠራቀምበት መሆኑ እና ፈሳሹ የሚመጣበት ክፍት ቦይ)**

- በተጨማሪም ሳታሳይ፣ ደፕሬም ቢዝነስ ኤደን ሮዝ፣ የፍሳሽ ቆሻሻውን ምንጭ፣ መጠንና እና ባህሪ በማወቅ እንዲሁም በመመርመር ለሚመነጨው ቆሻሻ አይነት የፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ ቴክኖሎጂ የሌለውና ደረቅ ቆሻሻ የሚቃጠልበት የደረቅ ቆሻሻው የተለየ ቴክኖሎጂ(incinerate) የሌለውና ደረቅ ቆሻሻውን ክፍት ቦታ ላይ በማቃጠል እያስወሰገዱ መሆኑ፤




ፎቶ-8 ኤደን ሮዝ ቆሻሻ በሜዳ ላይ የሚቃጠል መሆኑ

- እንዲሁም፤ ከኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ አከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መረጃ መሰረት በአበባ እርሻዎች ደረቅ ቆሻሻዎች በየቦታው እየተጣለ ከብቶች እየተመገቡ ጉዳት እየደረሰባቸውና የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ ወጥ በሆነ መልኩ እያስወገዱ እንዳልሆነ ታውቋል፡፡

153. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ አዎ በቆሻሻ አያያዝ ላይ ክትትል አላደረግንም ለወደፊት የሚሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

154. እንዲሁም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ተግባሩ የፌደራል እና የክልል አከባቢ ጥበቃ ሲሆን፤ በሚ/ር መ/ቤቱ ቀደም ሲል የነበረዉ የግብርና አከባቢ ጥበቃ መዋቅር እንዲፈርስ በመደረጉ ተቀናጅቶ ለመስራት አስቸጋሪ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

155. በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ቆሻሻን ከምንጩ ከመቀነስ አንፃር፣ ቆሻሻ ከተፈጠረ በኋላ በዓይነቱ ተለይቶ ከማስወገድ አንፃር የተሰሩ ስራዎች (የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ (ጉድጓድ፣ ስርዓቱን የጠበቀ ማቃጠያ፣ ቦይ፣ ሴፕቲክ ታንክ ወዘተ) ተመልሰው ጥቅም ለማይሰጡ ቆሻሻዎች ጊዜያዊ ማከማቻና ማስወገጃ ቦታ

ስለመዘጋጀቱ፣ ተመልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ ተረፈ ምርቶች በህጋዊ መንገድ ለተገቢ ጥቅም እንዲውሉ ስለመተላለፋቸው እና ጥቅም ላይ የማይውሉና ባዶ የኬሚካል መያዣ እቃዎችን በአግባቡ (በአዋጅ ቁጥር 513/1999) መሰረት ስለመወገዱ ጋር በተያያዘ የድጋፍ፣ ክትትልና የማብቃት ስራ በመሰራት ላይ ሲሆን የቁጥጥር ስራን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተግባርና ሃላፊነት አለመሆኑ ግንዛቤ መወሰድ እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

156. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ድጋፍ፣ ክትትልና የማብቃት ስራ የሰሩበትን የክትትል ሪፖርት እና የማብቃት(ግንዛቤ መስጫ )የተሰጠበት ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ስላልቀረበልን ስራው ተሰርቷል ብለን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

157. ሆኖም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአበባ እርሻ ድርጅቶቹ የሚወጡ ቆሻሻዎች በሚከማችበት፣ በሚጓጓዝበት፣ በሚወገድበት ጊዜ በደንቡ መሠረት የመዋቅር አደረጃጀት በመዘርጋት ተግባራዊ አለማድረጉ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

158. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአበባ እርሻ ድርጅቶቹ የሚወጡ ቆሻሻ በሚከማችበት፣ በሚጓጓዝበት፣ በሚወገድበት፣ ጊዜ ቆሻሻ በአግባቡ መያዝና መወገዱን የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ባለመስራቱ ከድርጅቱ የሚወጣው ቆሻሻ በሚወገዱበት ወቅት በሰራተኛ፣ ጤናና በአከባቢ ላይ እንዲሁም በከርሰ ምድር ውሃ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡

**የማህበራዊና የአከባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎችን አሟልተው እየሰሩ ስለመሆናቸው ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፡**

159. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ እርሻ ልማት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች የማህበራዊና የአከባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎችን አሟልተው እየሰሩ ስለመሆናቸው ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሊከታተል ይገባል።

160. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩት የአበባ እርሻ ድርጅቶች፣

- የተደነገጉት ዝቅተኛ የአከባቢ እና ማህበራዊ ግዴታዎች ማለትም የነሀስ ደረጃ መስፈርቶችን (ከአከባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ ቆሻሻ አያያዝ ስርዓትን መከተል፣የአከባቢና የስራ ቦታ ደህንነት ጠንቆችን መገምገም፣ ደህንነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ንጥረ ነገሮችን ማከማቸትን፣የተባይ ተቆጣጣሪ ሰራተኞች በግብርና ንጥረ ነገሮች

አያያዝና አጠቃቀም የሰለጠኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ ወዘተ..) የማያሟሉና በተፈለገው ሁኔታ እየተገበሩ ስለመሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀጉን ጠብቀው እንዲሰሩ የተደረገ ድጋፍና ክትትል የሌለ መሆኑ፤

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ እርሻ ልማት/ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ልማታቸውን ከአከባቢ ምቹ በማድረግ እና በአለም ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የተቀመጡትን የነሀስ፡ የብር፡ የወርቅ ደረጃ ለደረሱት እውቅና እየተሰጠ የሚካሄድበትን ስርአት ለመዘርጋት ያቀደ ቢሆንም፤ በዕቅዱ መሰረት እውቅና እንዲሰጣቸው የተደረገ ድጋፍና ክትትል የሌለ መሆኑ፤
- በሚመለከተው የመንግስት አካል ባወጣ ስታንዳርድ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር አምራችና ላኪዎች ማህበር በተነሳሽነት ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት እና እንደ ሀገራች ነባራዊ ሁኔታ በመንግስት አካል ኦዲቱን እንዲሰሩ እውቅና ባልተሰጣቸው በኮንትሮል ዩኒየን ኢትዮጵያ(control union Ethiopia) ኦዲት እየተደረጉ የአከባቢ እና ማህበራዊ ግዴታዎች አሟልቷል ተብሎ ሰርተፍኬት እየተሰጣቸው መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የማህበራዊና የአካባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎችን ሊመዘንበት በሚያስችል መልኩ ስታንዳርድ እንዲወጣ በማድረግ በስታንዳርዱ መሰረት በመንግስት አካል የአከባቢ ኦዲት ፈቃድ በተሰጣቸው አካላት ኦዲት እንዲያስደርጉ እንዲሁም በትክክል የማህበራዊና የአከባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎችን አሟልተዋል ተብሎ የኦዲት ሪፖርት ሲቀርብ ስለትክክለኛነቱ ሰርተፍኬት በሚሰጠው አካል ተረጋግጦ ሰርተፍኬት እንዲሰጥ የድጋፍና የክትትል ስራ ያልሰራ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

161. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ለባለሀብቶች የማህበራዊና የአከባቢያዊ ደረጃዎችን ጠብቀው ሰርተፍኬት ማግኘታቸው ተከታትለን እየሰራን አይደለም ለወደፊት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ

አካለት ጋር በመሆን እናስተባብራለን ሲሉ ስታንዳርድ ማውጣቱ ላይ ችግር እንደለባቸውና በመስሪያ ቤቱ አደረጃጀት ምክንያት ሊሰሩ እንዳልቻሉ እና ለወደፊት እንደሚሰሩት ገልጸዋል፡፡

162. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ቀደም ሲል የነበረዉ የግብርና አከባቢ ጥበቃ መዋቅር እንዲፈርስ በመደረጉ ተቀናጅቶ ለመስራት አስቸጋሪ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

163. በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምልሽ ይህ ተግባር የሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመሆኑ ግንዛቤ መወሰድ እንዳለበት ገልጸዋል።

164. የሚኒስቴር መ/ቤት የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአስር አመት መሪ እቅድ በሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶችል ምርታቸውን ከአካባቢ ጋር በተዋደደ አግባብ እንዲያካሂዱና በአለም ገበያ ተወዳደሪ እንዲሆኑ በአለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የነሃስ (Bronze)፣ ብር (siliver) እና ወርቅ(Gold) ደረጃ ለደረሱት እውቅና እየተሰጠ የሚሄድበት ስርዓት ዘርግቶ ለመስራት ያቀደ ሆኖ ሳለ ይህ ተግባር የሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመሆኑ ግንዛቤ መወሰድ አለበት ተብሎ የተሰጠው ምልሽ ተቀባይነት የለውም፡፡

165. ዘርፉን የሚመሩት የሥራ ሀላፊዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚሰራውን ስራ የሌላው አካል ድርሻ ነው ብሎ በማሰባቸውና በቅንጅት አለመስራታቸው እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፤

166. በመሆኑም ባለሀብቶች የማህበራዊና የአካባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎችን አሟልተው እየሰሩ ባለመሆናቸው በስነምግባር ደንብ የተደነገጉ ዝቅተኛ የነሀስ ደረጃ መሟላት ያለበት ስታንዳርድ ሳያሟሉ ሰርተፍኬት እየተሰጣቸውና እንዲሁም በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት እንዳይሰሩና መጠበቅ ያለበትን አካባቢና ማህበረሰብ ደረጃዎች እንዳይጠበቅ አድርጓል፡፡

### ለአልሚዎች የተላለፈው መሬት አጠቃቀም በተመለከተ

167. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአበባ እርሻ ልማት ዙሪያ ጠንካራ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ለአልሚዎች የተላለፈውን መሬት ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ የመሬት ብክነትን ሊያስወግድ ይገባል።

168. የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን ደንብ ቁጥር 396/2017 አንቀፅ 3 ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለአበባ እርሻ

የሚሆኑ መሬቶች በጥናት ለይቶ እንዲሰጥ በማድረግ ለአልሚዎች የተላለፈውን መሬት ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ የመሬት ብክነትን ሊያስወግድ እንደሚገባ ሀላፊነት ተሰቶታል፡፡

169. ይሁን እንጂ ለኦዲት ቡድኑ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካለት እንዲሁም ከአበባ እርሻ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ- መጠይቅ ለመረዳት እንደተቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአበባ እርሻ ልማት ዙሪያ ጠንካራ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ለአልሚዎች (ኩባንያዎች) የተሰጣቸውን መሬት በአግባቡና አሟጠው በመጠቀም የመሬት ብክነትን ለማስወገድ ድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

170. ለአብነትም

- አበባን ሲያመርቱ የነበሩት ስድስት ኩባንያዎች ( ኦምኒ ብሎሶም፣ሬንቦ ከለር፣ ሱፐር ፍሎሪካልቸር፣ ጆፍላወር ፣አግሪ ፍሎራ፣ሸሚ ፍሎራ) የአበባን ምርት ከማምረት ወደ ሌላ ሆልቲካልቸር ሰብል ማምርትና ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀርብ ችግኝ በማፍላት ስራ ላይ በመሰማራታቸው (በመቀየራቸው) በአበባ ልማት የሚሸፈን መሬት በመቀንሱ በአጠቃላይ ከ148 ሄክታር መሬት በአበባ እንደማይለማ ወይንም 32,915 ቶን የአበባ ምርት ከነባሩ ማሳ ላይመረት እንዳይችል ማድረጉ፣
- የመሬት አጠቃቃም መደበኛ ስራ ወጥ በሆነ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት(ስለሚቀያየሩ) በተከታታይነት ያለመከናወኑን እና አዲሱ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ስላለፈው እቅድና አፈጻጸም በቂ መረጃ የሌላቸው መሆኑ፣
- በከተማ መሬት አስተዳደር ስርዓት የአበባ እርሻ ልማት ያገናዘበ የሊዝ ጊዜንና ተመንን በተመለከተ የተዘጋጀ መመሪያ አለመኖር፣
- በተጨማሪም በናሙና ተመርጡው በታዩ ክልሎች የአካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች፣ እንዲሁም ከአበባ እርሻ ድርጅት ከስራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ኢንቨስትመንት(ደቡብ ም/ሸዋ-በወሊሶ) 376 ሄክታር፤ (ም/ሸዋ-ሆለታ) 117፤ ጉናትሬዲንግ (ሰበታ) 20 ሄክታር እናመሀመድ ኢብራሂም(በቢሾፍቱ) 10.5 ሄክታር ፡አሰላ ፍለወር 2.5 ሄክታር፡ሳሮን ሮዝ 4 ሄክታር ፡ዲፕሪም ቢዝነስ በ79 ሄክታር፡ቲናው ቢዝነስ

15 ሄክታር ፡አቢሲኒያ ፍላወር 22.5 ሄክታር፡ድሬ ባይ ኮላር 16.5 ሄክታር በአጠቃላይ 662.8 ሄክታር የሚሆን መሬቱን ተረክበው የአበባ ምርቱን እየተመረተበት እንዳልሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡(ዝርዝሩ በአባሪ 4 ተያይዟል)

171. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በባንክ ዕዳ ተይዘውና በፀጥታ ምክንያት እንዳላለሙና በመሬት አጠቃቀም ላይ ከክልሎች ጋር ተቀናጅተው እየሰሩ እንደሆነና መሬት የመስጠት እና የማስተዳደር ስልጣን የክልሎች ሀላፊነት ስለሆነ ያልለሙ መሬቶችን ወደ መሬት ባንክ እያስገቡ ሲሆን እንደ ግብርና ሚኒስቴር የቴክኒክ ድጋፍ እያደረጉ መሆኑንና የወሰዱትን መሬት እንዲያለሙ ኤክስፖርቱን ከማበረታታት አንጻር በተደጋጋሚ ከክልል ጋር ሲሰራ ነበር አሁንም አስፈላጊዉን ድጋፍ ሲጠይቁ ተቀናጅተው እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

172. በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ መሬት የመስጠት እና የማስተዳደር ስልጣን የክልል ቢሆንም የወሰዱትን መሬት እንዲያለሙ ኤክስፖርቱን ከማበረታታት አንጻር በተደጋጋሚ ከክልል ጋር በቅንጅት በመሰራት ላይ ሲሆን በቀጣይም አስፈላጊዉን ድጋፍ ክልሎች ጋር በመቀናጀት እንደሚሰራ ገልጸዋል።

173. የአበባ ዘርፉን የሚመሩት የሥራ ሀላፊዎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለአልሚዎች (ኩባንያዎች) የተሰጣቸውን መሬት በአግባቡና አሟጠው በመጠቀም የመሬት ብክነትን ለማስወገድ ጠንካራ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ክትትል አለማድረጉ እንደምክንያት ይጠቀሳል፡፡

174. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የአበባ ምርት አልሚዎቹ የተሰጣቸውን መሬት በአግባቡ ስለመጠቀማቸው ክትትልና ድጋፍ ባለማድረጋቸው ምርት ሊሠጥ የነበረው መሬት የባከነና ለሌላ አገልግሎትም እንዲውል ስላልተደረገ፤ ከዘርፉ መንግስት ማግኘት የሚገባውን ምርትና ገቢ እንዲቀንስ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## የአበባ እርሻ ልማት ግብይት ወቅታዊ፣ የምርትና የግብይት መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረጉን በተመለከተ

175. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ግብይት ወቅታዊ፣ ሀገራዊና አለም አቀፋዊ የምርትና የግብይት እንዲሁም ተያያዥ መረጃዎችን ሊሰበስብ፣ ሊያደራጅ፣

ሊተነትንና በወቅቱም ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ሊያደርግና ተፈጻሚነቱን ሊከታተል ይገባል።

176. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት፤ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአበባ እርሻ ዘርፍ በቂና ግልፅ መረጃ ልውውጥ እንዲኖር የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ እንድዘረጋ በማድረግ ወቅታዊ፣ ሀገራዊና አለም አቀፋዊ የምርትና የግብይት እንዲሁም ተያያዥ መረጃዎችን በመሰበሰብ፣ በማደራጀት፣ በመተንተንና በወቅቱም ለተጠቃሚዎች ተደራሽ በማድረግ ተፈፃሚነቱን ያልተከታተለ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለአብነት፤-

- የሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ልማት መረጃ አያያዝና ስርጭት በግለሰብ ደረጃ/ በሰራተኛ የተያዙ በመሆኑ የሚፈለገውን መረጃ በቀላሉ ለማግኘት፤ እንዲሁም ከክልል የሚመጣ መረጃ በኢንፎርሚሽን ሲስተም የተደገፈ መረጃ ግንኙነት የሌለው መሆኑ፤
- ለአበባ እርሻ ዘርፍ በቂና ግልፅ መረጃ ልውውጥ እንዲኖር የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አለመኖር፣ ያሉትን ቴክኖሎጂዎች ለመጠቀም ያለው የግንዛቤ ማነስ፣ ስለቴክኖሎጂው አሰራር የመረጃ እጥረት መኖር፤ የሀገር ውስጥና ኤክስፖርት ገበያ መረጃ ላይ ግልፅነት ማነስ፤ የኤክስፖርት ገበያ መረጃ በተጠናከረ መልኩ አለመደራጀትና የተደራሽነት እጥረት መኖር፤

177. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ኤክስፖርት መረጃ በየወሩ በጠቅላይ ሚኒስትር የሚገመገም ሲሆን፤ ነገር ግን ምን ያክል ምርት ተመረተ፣ ምን ያክል መጠን ወደ ውጪ ተላከ የሚለውን በየኩባንያዎቹ መረጃ የምንለዋወጥበት የመረጃ ልውውጥ ቴክኖሎጂ ስርአት ገና እየሰሩ እንደሆነና ለወደፊት መረጃ ተጠናክሮ የሚሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

178. በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ይህ ቀደም ሲል የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በነበረበት ወቅት በቂ ልምድ የሀገር ዉስጥ እና የውጭ ተሞክሮ ተወስዶ ሲሰራበት የቆየ የነበረ ቢሆንም፤ አደረጃጀቱ በተደጋጋሚ በመቀያየሩ በሚፈለገው አግባብ ማስኬድ እንዳልተቻለ ግንዛቤ ቢወሰድ በማለት ገልጸዋል።

179. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአልሚ ድርጅቶቹ፣ ከገዥ ድርጅቶቹ እንዲሁም መረጃውን ለማወቅ ከሚፈልጉት ባለድርሻ አካላት ጋር ሊያገናኘው የሚያስችል በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለመዘርጋቱ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

180. በመሆኑም በዘመናዊ መልኩ መረጃ ተደራጅቶ ለተጠቃሚውና ለአበባ እርሻ ድርጅቶች ባለመድረሱ የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም፣ ኤክስፖርት ገበያ መረጃ ላይ ግልፀኝነት፣ ታማኝነት እንዳይኖረው አድርጓል፤እንዲሁም መረጃውን የሚፈልጉ አካላት በቀላሉ እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

**ከሀገር ውስጥና ከውጪ ተሞክሮዎችን በመቀመር ቋሚ የምክክር መድረክ ማዘጋጀቱን በተመለከተ**

181. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ስራዎችን ፈጣን እድገትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ ተሞክሮዎችን በመቅሰም፤ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበትን ቋሚ የምክክር መድረክ በማመቻቸት የልምድ ተሞክሮችን በመቀመር ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

182. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ስራዎችን ፈጣን እድገትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ ተሞክሮዎችን በመቅሰም፤ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበትን ቋሚ የምክክር መድረክ በማመቻቸት ልምድ ልውውጥ ያላደረገና የተቀመረ የልምድ ተሞክሮ የሌለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

183. በሌላ በኩል በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቅሰም የመቀመርና የማስተላለፍ ልምድ የማነስ ችግር ያለ እንደሆና እንዲሁም የሰው ኃይል ስልጠና እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች አለመዳበሩ፤

184. በተጨማሪም በሲዳማ ክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በተገኘ መረጃ፣ የልምድ ልውውጥ እና የምክክር መድረክ በበቂ ሁኔታ አለመኖሩ፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎቹን ባለሙያ በተሻለ ሁኔታ አውቀው ድርጅቶችን ለመቆጣጠር እና ለመከታተል የክህሎትና የልምድ ማነስ ክፍተት እንዳለ ታውቋል፡፡

185. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ የልምድ ልውውጥ እና ተሞክሮ በመቅሰም የባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ምክክር ማድጋቸውን፣ መልካም ተሞክሮዎችን ከአንዱ አበባ አምራች ወደ ሌላው አምራች ልምድ የመቅሰም ስራ እንደሰሩና ቀደም ሲል

የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በነበረበት ወቅት በቂ ልምድ የሀገር ዉስጥ እና የዉጭ ተሞክሮ ተወስዶ ሲሰራበት የቆየ የነበረ ቢሆንም ኤጀንሲዉ በመፍረሱ እና በተደጋጋሚ በተለያየ መወቅር በመደራጀቱ ከቴክኖሎጂ መለዋወጥ አንጻር ተጨማሪ ተሞክሮ በመቀመር እንደሚስፋፋ ገልጸዋል፡፡

186. በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ ቀደም ሲል ዘርፉን በሚመለከት የሀገር ዉስጥ እና የውጭ ተሞክሮ ተወስዶ ሲሰራበት የቆየ የነበረ ቢሆንም አሁን ግን በተፈለገው አግባብ መሄድ ያልተቻለ ሲሆን በቀጣይ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

187. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ ዘርፍ የሚደግፍበት መዋቅር እንዲሁም የተሞክሮ ቅመራና ልምድ ልውውጥ ሥርዓት አለመዘርጋቱና ተቀናጅቶ መስራት ላይ ክፍተት በመፍጠሩ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

188. በመሆኑም በአበባ እርሻ ልማት ስራዎችን ፈጣን እድገትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ ተሞክሮዎችን በመቅሰም፤ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበትን ቋሚ የምክክር መድረክ እና የተቀመረ መልካም ተሞክሮ ባለመኖሩ ዝቅተኛ አፈፃፀም እና ልምድ የሌላቸው የአበባ እርሻ ድርጅቶች ከነበሩበት አሰራር በተሻለ መልኩ እንዳይሰሩ አድርጓል፡፡

**ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋቱን በተመለከተ**

189. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ አልሚ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲያወጡ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን እንዲሁም ከአከባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ሊሰራ እና ሊከታተል ይገባል፡፡

190. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ አልሚ ባለሀብቶች ፈቃድ ሲያወጡ ጀምሮ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት (ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን እንዲሁም ከአከባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እና ክልልሎች) ጋር ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት ሰነዶችና በኦዲቱ ወቅት ቃለ-መጠይቅ ከተደረገላቸው ባለድርሻ አካላት ለማወቅ ተችሏል፡፡

191. እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት ላይ ትልቅ ክፍተት እንዳለና ባለሀብቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲመጡ የሚሰራው ፕሮሞሽን በራሱ ክፍተት ያለበት መሆኑ፤ ይኸውም ርካሽ የሰው ሀብት፣ ከታክስ ነፃ ፣ የአካባቢ ክፍያ የለም

ተብለው፣ባለሀብቶቹ ወደ ሀገር እንዲመጡ መደረጉ አልሚ ባለሀብቶች ለአካባቢ ጥበቃ የሚሰጡት ትኩረት አናሳ እንዲሆን ያደረገ መሆኑ፣

192. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ግብርና ሚ/ር ኢንቨስትመንት የሚደግፍበት መዋቅር ስላልነበረ ተቀናጅቶ መስራት ላይ ክፍተት እንደፈጠረባቸውና በአሁኑ ግን መዋቅሩ ኢንቨስትመንት በቀጥታ ፈቃድ ከማግኘት ጀምሮ እስከ ልማት እየደገፉ እንዳሉና የባለድርሻ አካላት ፎረም ስለተቋቋመ በዚያ መልኩ የቅንጅት አሰራር እንደዘረጉ ገልጸዋል፡፡

193. የበላይ ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ በአሁኑ ፈቃድ ከማግኘት ጀምሮ እስከ ልማት እየደገፉ እንዳሉ የገለጹ ቢሆንም በዚህ መልክ እየሰሩ እንዳሉ የሚሳይ ማስረጃ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ስላልቀረበ የተሰጠውን ምለሽ የኦዲት ቡድኑ ለመቀበል ይቸገራል፡፡

194. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ አልሚ ድርጅቶቹ በምርት ሂደት በአከባቢ ላይ የሚደርሰውን ተፅጽኖ ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲያወጡ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ አለመስራቱ እንደ ምክንያት ይጠቀሳል፡፡

195. በመሆኑም ተቀናጅቶ ባለመሰራቱ የአበባ እርሻ ኢንቨስትመንቱ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲሰጥ የአከባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ይሁንታ ሳያገኝ ፈቃድ የሚሰጥ ሲሆን፣ የግብርና ሚኒስቴር ደግሞ በትክክል የአካባቢ ተፅጽኖን ያላስገመገመ እና ተፅጽኖውን የሚያስቀንስበት የአካባቢ ማገገሚያ ዕቅድ ያላዘጋጀውን የአበባ አልሚ ድርጅቶች በመቀበል ልማቱን እንዲመራ ተደርጓል፡፡

እነዚህን ከላይ የተመለከቱት ግኝቶችና የተሰጡትን ምላሽ በመተንተን የተደረሰበት የመደምደሚ ሀሳቦች ቀጥሎ በክፍል ሶስት ቀርቧል፡፡

# ክፍል ሶስት

***መደምደሚያ***

196. ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው የአበባ እርሻ ልማት ምርታማነት አፈፃፃምና የአከባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነት አፈፃፀምን በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎች፣ ዞኖች፣

የመንግስት ተቋማት፣ የግል ተቋማትና በአበባ እርሻ ድርጅቶች የታዩ ግድፈቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

- ✓ የግብርና ሚኒስቴር የአበባ እርሻ ልማት ፈጣን እድገትና ቀጣይነትን ለማረጋገጥ እና በአከባቢው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የሚረዱ የህግ ማእቀፎች (ፖሊሲ መመሪያዎች፣ ስትራቴጂዎች፤ ፍኖተ ካርታ፤ስታንዳርድ/ጋይድ ላይኖች) ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በረቂቅ ደረጃ እንዳሉና ጸድቀው ወደ ሚመለከታቸው አካል (የአበባ እርሻ ድርጅት) እንዲወርድ ያልተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም የአበባ እርሻ ምርቶች ከብክነት፡ በአከባቢ እና በኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳያስከትሉ የኮንሶሊዴሽን የህግ ማዕቀፍ መመሪያ በረቂቅ ደረጃ ያለውን አጸድቆ ተግባራዊ አላስደረገም፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አጋርነትን በመፍጠር በሀገር አቀፍ ደረጃ የአበባ እርሻ ለማልማት የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች በተፈጥሮ ሀብት፣በሰው፣ በእፀዋት እና በእንሰሳት ላይ የሚያስከትለውን ችግር ለመለየት እና ሊፈጠር የሚችለውን ችግር በመረጃ አውቆ ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ በጥናት ላይ የተመሠረት ሥራ አልሰራም፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአበባ እርሻ ልማቱ የሚያስፈልጉትን የኬሚካሎች መጠንና ዓይነት ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲገዛና እንዲሰራጭ የሚጠቀሙትን ኬሚካሎች በተገቢው መንገድ እንዲጓጓዙና እና በተገቢው መጋዘኖች ውስጥ እንዲከማቹ ተገቢውን የድጋፍና የክትትል ስርዓት ዘርግቶ እየሰራ አለመሆኑ፤
- ✓ ከአበባ እርሻ ድርጅቱ የሚወጣው ቆሻሻ በአግባቡ ተመርምሮና ክትትል ተደርጎበት እንዲሁም የአበባው ምርት ላይም ሆነ ተረፈ ምርቶች ላይ ያለው ኬሚካል ቅሬት መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ ላብራቶሪ እንደሀገር የሌለና  የላብራቶሪ ምርመራ እንዲያስድርጉ ለማድረግ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ እየሰራ አለመሆኑ፤
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ ልማት ዘርፍ የሚከሰቱት ማነቆዎችን (የቅዝቃዜ ሰንሰለት((cool of chain) የኤለክትሪክ አቅርቦት፤ የስልክና የኢንትርኔት አውታሮች ፡የሊዝ ክፍያ ተከፍሎ የመሬት ባለቤትነት(ባለይዞታነት) አላማግኘት ችግር በዘላቂነት  ለመፍታት (ለመቅረፍ) ያካሄደው ጥናት የሌለ መሆኑ፤

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኢንቨስትመንት፣ለኢንዱስትሪ፣ ለመኖሪያነት መዋል አለበት የሚለውን መሬት ለመለየት ኢንቨስትመንቱን ለማስፋፋት ጥያቄ ለሚያቀርቡት ምላሽ ለማግኘት የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ በረቂቅ ደረጃ እንደለና አፀድቆ ተግባራዊ እንዲሆን አላደረገም፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአከባቢ ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት ሁሉን አቀፍ እና የተሳለጠ ለማድረግ መመሪያዎችን፡ ማኖዋሎችን በማዘጋጀት አፀድቆ ተግበራዊ አላደረግም፤ እንዲሁም የስነ ምግባር ደንቡ አፈፃፀም ብቁ እና ቀልጣፋ ለማድረግ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የስልጠና፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የማስተዋወቅ ስራዎችን በተከታታይነት አልሰራም፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተከለከሉና ጊዜው ያለፈባቸው የፀረ-ተባይ የአወጋገድ መመሪያ አዘጋጅቶ አፀድቆ ተግባራዊ እንዲሆን የክትትልና የቁጥጥር የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በሰዎች፤ በእንሰሳትና በአከባቢ፤እንዲሁም ለአየር መበከል አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳይፈጥር፤በሚታየው ችግር ልክ ለተፈጻሚነቱ አልሰራም፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የውስጥ እና የውጪ የአከባቢ ኦዲት እንዲያስደርጉ የድጋፍ የክትትል ስርአት ዘርግቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አምራቾች አበባውን ለማምረት የሚጠቀሙት ግብዓት ወደ ከረሰ ምድር ውስጥ እንዳይገባ የፕላስቲክ ንጣፍ እንዲጠቀሙ እንዲሁም ምርቱን ለማምረት የተጠቀሙት ግብአት በአፈር ውስጡ ምን ያክል ቅሬት አለው የሚለውን ምርመራ እንዲካሄዱና የማከም ስራ እንዲሰሩ የድጋፍና ክትትል ስራ አልሰራም፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለአበባ እርሻ እና ለሌሎች እርሻ የሚውለው መሬት በጥናት ልየታ በማድረግ መሰረታዊ መረጃዎችን በማደራጀት ወደ መሬት ቋት እንዱገቡ እና ለባለሀብቶች እንዲሰጥ አላደረገም፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የውሃ ፍጆታ/መጠን፣ የግብርና ግብዓቶች/ፀረ አረም እና ፀረ ተባይ/ ፀረ ፈንገስ እና ማዳበሪያ አጠቃቀሙን፣ ጥቅም ላይ የሚውል የኃይል ምንጭ እና ፍጆታውን መዝግቦ ባለመያዙ በአመት ምርቱን ለማምረት ምን ያክል ፍጆታ እንደሚጠቀሙ የድጋፍና የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ለተግባራዊነቱ የክትትል ስራ አልሰራም፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻዎች ልማቱን ሲያለሙ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ቀርፆ ውጤታማነታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ እየሰራ አለመሆኑ፣
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለዉ የመልካም እርሻ አተገባበር ሥርዓት(ዘላቂ የአከባቢ ከመጠበቅ የሰራተኛን መብት ከመጠበቅ የስራ ቦታ ደህንነትና ጤንነት ከመጠበቅና ድርጅቶቹ ከአካባቢ ማህበረሰብ ጋር ተስማምቶ ምርትና ምርታማነቱን እንዲጨምር የአመራረት ሥርዓቶች ተግባራዊ እንዲሆን አላደረገም፡፡
- ✓ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅት የሚጠቀሙት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ግብዓቶች ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ ስለማይገቡ ድርጅቶቹ ከፍላጎታቸው በላይ በማስገባት ፀረ-ተባይ ኬሚካሉ በአበባ እርሻ ድርጅቱ ውስጥ እንዳይከማችና ለሕገወጥ የኬሚካል ንግድ በር እንዳይከፍት የክትትል ስርአት በመዘርጋ ክትትልና ቁጥጥር አላደረገም፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካለት ጋር በመሆን የአበባ እርሻ ልማቱ ሊኖረው የሚችለውን ተፅዕኖ ለመለየትና ለመገምገም የአከባቢ ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ (ESIA) አቅርበው እንዲገመገም፤ የማህበራዊና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ (Environmental management plan) አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ በመርዳት የአከባቢና ማህበረስብ ደህንነት በጠበቀ መልኩ ድርጅቶቹ ልማቱን እንዲያለሙ የድጋፍና ክትትል ስራ አልሰራም፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች አካባቢ ከመጠበቅ አንፃር የተቀናጀ ተባይ መከላከል /IPM/ እንዲተገብሩ ድጋፍና ክትትል ስራ አልሰራም፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካል ጋር በመሆን በአበባ እርሻ ድርጅት ውስጥ ለሚሰሩት ሰራተኞች፤በተለይ ለሴት ሠራተኞች ሀገራዊና እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች፣ የስራ አከባቢ ምቾትን ከስራ ጋር ተዛማች የሆኑ ስልጠናዎች፤ የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች እንዲሁም የጤና ምርመራ ድንጋጌዎች መሰረት የሰራተኛን የሰብኣዊ መብት መከበሩን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት አልተከታተለም፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ከአበባ እርሻ ድርጅቶቹ የሚወጡ ቆሻሻዎች የሚመከማችበትን፣ የሚጓጓዝበትን፣ የሚወገድበትን ስርዓት በመዘርጋት በሰዎችና በእንስሳት ጤና እና በአከባቢ ብክለት በማያስከትል መልኩ ቆሻሻ በአግባቡ እንዲያዝና እንዲወገድ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ክትትልና ድጋፍ አላደረገም፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአበባ እርሻ ድርጅቶች የማህበራዊና የአከባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎችን ሲያሟሉ ስለትክክለኛነቱ ሰርተፍኬት በሚሰጠው አካል ተረጋግጦ ሰርተፍኬቱ ለአምራቾች እንዲሰጥ የድጋፍና የክትትል ስርዓት በመዘርጋት አልተከታተለም።

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአበባ እርሻ ልማት ዙሪያ ጠንካራ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ለአልሚዎች የተላለፈውን መሬት ውጤታማ እንዲሆንና ያልለማ መሬት ወደመሬት ባንክ በመመለስ መሬቱን ከብክነት ለመከላከል የክትትል ስርአት በመዘርጋት አልተከታተለም።

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ግብይት ወቅታዊ፣ ሀገራዊና አለም አቀፋዊ የምርትና የግብይት እንዲሁም ተያያዥ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት፣በመተንተንና በወቅቱም ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ፤ እንዲሁም አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ ሶፍትዌር በመፍጠር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ሥርዓትን በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን ክትትል በማድረግ ተፈጻሚነቱን አልተከታተለም።

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ እርሻ ልማት ስራዎችን ፈጣን ዕድገትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የምክክር መድረክ በማመቻቸት ተሞክሮችን በመቀመር የልምድ ልውውጥ ለማድረግና ለማስፋት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን አቅም ለመገንባት የሚያስችል ወጥነት ያለው መድረክ በማመቻት ተግበራዊነቱን አልተከታተለም፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአበባ አልሚ ባለሀብቶች የሚያስፈልጉትን ከኢንቨስትመንት ፈቃድ ማውጣት ጀምሮ እስከ ምርት ማምረትና መሸጥ ድርስ ላለው ሂደት

ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቀጠይነትና ተከታታይነት ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ለተፈፃሚነቱ አልሰራም ፡፡

ከላይ በተጠቀሱት የመደሚደሚያ ሀሳቦች በመነሳት ተግባራዊ ቢደረጉ ችግሮቹን ሊቀርፉና በቀጣይነት በአከባቢ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ስጋቶችን በመቀነስ የአበባ እርሻዎችን ምርታመነት ሊያሰድጉ ይችላሉ ያልነቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች በክፍል አራት ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

## *የማሻሻያ ሃሣቦች*

197. ከላይ በተደረሰው መደምደሚያ ሀሳቦች መሰረት የግብርና ሚኒስቴር የአበባ እርሻ ልማት ምርታማነት ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎች በሀገራችን የተፈለገውን ውጤት በሚያመጣ መልኩ እየተሠራ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ በዝርዝር ለቀረቡት የኦዲት ግኝቶች መፍትሄ ይሆናሉ ያልናቸው የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ✓ ግብርና ሚኒስቴር የአበባ እርሻ ልማት፣ ፈጣን ዕድገትና ቀጣይነትን ለማረጋገጥ እና በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የሚረዱ የህግ ማእቀፎች (ፖሊሲ፣መመሪያዎች፣ስትራቴጂዎች፤ፍኖተ ካርታ፤ ስታንዳርድ(ጋይድ ላይኖች) እና የኮንሶሊዴሽን የህግ ማዕቀፍ መመሪያ ጭምር አዘጋጅቶ በስራ ላይ ማዋል እንዲሁም ቀደም ብለው የወጡና ማሻሻያ ያልተደረገላቸው የህግ ማዕቀፎችን በአተገባበር ላይ የሚፈጥሩትን ክፍተት በጥናት በመለየትና በመገምገም ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን እንዲሻሻሉ በማድረግ በመደገፍና በማስተባበር ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አጋርነትን በመፍጠር በሀገር አቀፍ ደረጃ የአበባ እርሻ ለማልማት የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች በተፈጥሮ ሀብት ፡በእፀዋትና በእንሰሳት ላይ ችግር እንዳያመጣ፤ከእርሻዎቹ የሚለቀቁትን ፈሳሽ ቆሻሻ  በገለልተኛ አካል የላብራቶሪው ናሙና ተወስዶ ችግር እንደሌው በየወቅቱ እየተረጋገጠ ወደ አካባቢው ከሚለቀቅ የአበባ እርሻ ድርጅቱ መልሶ እንዲጠቀም የሚደርግበትን የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ ጥናት አካሂዶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ✓ ግብርና ሚኒስቴር ለአበባ እርሻ ልማቱ የሚያስፈልጉትን የኬሚካሎች ዓይነት፤ መጠንና ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲገዛ፤በአግባቡ እንዲመዘገብና እንዲሰራጭ በማድረግ የሚጠቀሙትን ኬሚካሎች በተገቢው መንገድ እንዲያጓጉዙና ደረጃቸውን በጠበቁ መጋዘኖች ውስጥ እንዲያከማቹ ተገቢውን ስርዓት በመዘርጋት ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአበባ እርሻ ድርጅቶች የሚወጣው ቆሻሻ በአግባቡ ተመርምሮና እንዲሁም በአበባው ላይ ያለው ኬሚካል ቅሬት መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ የላብራቶሪ ምርመራ እንዲያስድርጉ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ ልማት ላይ የሚከሰቱ ማነቆዎች በመለየት እና ጥናት በማካሄድ  በተካሄዱ ጥናቶች መሠረት የመጣውን ለውጥ የሚገመግምበት እና

የሚመዝንበት እንዲሁም የሚታዩት ክፍተቶች ውጤት በሚያመጣ መልኩ ለመቅረፍ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለኢንቨስትመንት፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለመኖሪያነት መዋል አለበት የሚለውን መሬት ለመለየት እና ኢንቨስትመንቱን ለማስፋፋት ጥያቄ ለሚያቀርቡት ምላሽ ለማግኘት የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ አዘጋጅቶና አፀድቆ ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአከባቢ ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት ደንቡን ሁሉን አቀፍ እና የተሳለጠ ለማድረግ መመሪያዎችን፣ማኖዋሎችን በማዘጋጀት ተግበራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መቤቱ የአበባ እርሻ አምራቾች የሚጠቀሙት የተከለከሉና ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በሰራተኛው፣ በአከባቢውና በእንሰሳት እንዲሁም በአየር መበከል ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይፈጥር የአወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀት እንዲወገድ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲደረጉ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአከባቢ ደህንነትን ከማረጋገጥ አኳያ (በአፈር፣በውሃ፣በብዝሃ ሕይወትና በአከባቢው ማሕበረሰብ ) ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያደርስ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የውስጥ እና የውጪ የአካባቢ ኦዲት በየወቅቱ እንዲያስደርጉ የድጋፍ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ አምሚዎች አበባውን ለማምረት የሚጠቀሙት ግብዓት ወደ ከርሰ-ምድር ውስጥ እንዳይገባ የፕላስቲክ ንጣፍ እንዲጠቀሙና ምርቱን ለማምረት የተጠቀሙት ግብአት በአፈር ውስጥ ምን ያክል ቅሬት እንዳለው ምርመራ እንዲያካሄዱ በማድረግ የማከም ስራ እንዲሰራ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ በትኩረት ሊከታተል ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርድቶች የውሃ ፍጆታ/መጠን፣የግብርና ግብዓቶች/ፀረ አረም፣ፀረ ተባይ/ ፀረ ፈንገስ እና ማዳበሪያ አጠቃቀሙን ጥቅም ላይ የሚውል የኃይል ምንጭ በአመት ምን ያክል ምርቱን ለማምረት

እንደሚጠቀሙ ለማወቅ ቀልጣፋ የምዝገባና የሪፖርት አቀራብ ስርዓት በመዘርጋት ለተግባራዊነቱ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ልማቱን ሲያለሙ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ቀርፆ ተግባራዊነቱን እና ውጤታማነቱን ቀልጣፋ የሆነ የድጋፍና የክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለዉ የመልካም እርሻ አተገባበር ሥርዓት (ዘላቂ የአካባቢ ከመጠበቅ፡የሰራተኛን መብት ከመጠበቅ፡የስራ ቦታ ደህንነትና ጤንነት እንዲጠበቅና ድርጅቱ ከአከባቢ ማህበረሰብ ጋር ተስማምቶ ምርትና ምርታማነቱን እንዲጨምርና የአመራረት ሥርዓቶች ተግባራዊ እንዲሆን የክትትል ስርአት ዘርግቶ ተፈጻሚነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶቹ የሚጠቀሙት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ግብዓቶች ከፍላጎታቸው/ከተፈቀደው በላይ የሆነ እንዳያስገቡ፤ ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የክትትል ስርአት በመዘርጋት ተፈጻሚነቱን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በአከባቢ ላይ የሚያስከተለው አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ተገምግሞ ውሳኔ የሚሰጥበትንና የማህበራዊና የአከባቢ አያያዝ ዕቅድ (Environmental management plan) አዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ የድጋፍና የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊነቱን በክትትል ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች አካባቢ ከመጠበቅ አንፃር የተቀናጀ የተባይ መከላከል /IPM/ እንዲተገበር ድጋፍ በማድረግ አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን አበባ እርሻ ድርጅት ውስጥ ለሚሰሩት ሰራተኞች ሀገራዊና እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች፣የስራ አከባቢ ምቹትን ከስራ ጋር ተዛማች የሆኑ ስልጠናዎች፤

የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች፤ እንዲሁም የጤና ምርመራ ድንጋጌዎች መሰረት የሰራተኛን የሰብአዊ መብት መከበሩን፤በተለይም ሴት ሠራተኞች ጤንነታቸውና እና የስራ ቦታ ደህንነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ሊከታተል ይገባል፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ከአበባ እርሻ ድርጅቶቹ የሚወጡ ቆሻሻዎች የሚመከማችበትን፣የሚጓጓዝበትን፣ የሚወገድበትን፣ ስርዓት ስለመዘርጋቱ፤ በሰዎችና በእንስሳት ጤና እና በአከባቢ ብክለት በማያስከትል መልኩ ቆሻሻ በአግባቡ እንዲያዝና እንዲወገድ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ሊከታተልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአበባ እርሻ ድርጅቶች የማህበራዊና የአከባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎችን ሲያሟሉ ስለትክክለኛነቱ ሰርተፍኬት በሚሰጠው አካል ተረጋግጦ ሰርተፍኬቱ ለአምራቾች እንዲሰጥ የድጋፍና የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአበባ እርሻ ልማት ዙሪያ ጠንካራ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ለአልሚዎች የተላለፈውን መሬት ውጤታማ እንዲሆንና መሬቱን ከብክነትን በመከላከል ያልለማ መሬት በወቅቱ ወደመሬት ባንክ እንዲመለስ/ለሌላ ልማት እንዲውል ለማድረግ የሚስችል የክትትል ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል።
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ግብይት ወቅታዊ፣ ሀገራዊና አለም አቀፋዊ የምርትና የግብይት እንዲሁም ተያያዥ መረጃዎችን በመሰበስብ፣ በማደራጀት፣ በመተንተንና በወቅቱም ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለመድረግ እንዲሁም አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ አሰራር በመፍጠር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ሥርዓትን በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን ክትትል በማድረግ ተፈጻሚነቱን ሊከታተል ይገባል።
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ እርሻ ልማት ስራዎችን ፈጣን ዕድገትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የምክክር መድረክ በማመቻቸት ተሞክሮችን በመቀመር የልምድ

ልውውጥ ለማድረግና ለማስፋት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የኢንቨስትሜንት ኮሚሽኑን፣ የክልል ተቋማትን፣ የባለሙያዎችንና አመራሮችን እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን አቅም ለመገንባት የሚያስችል ወጥነት ያለው መድረክ በማመቻት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ አልሚ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከማውጣት ጀምሮ እስከ ምርት ማምረት፤ማጓጓዝና መሸጥ ድረስ ላለው ሂደት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካል ጋር ቀጠይነትና ተከታታይነት ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

በመጨረሻም የግብርና ሚኒስቴር ሰራተኞችና የስራ ኃላፊዎች፤የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ኃላፊዎች እና የአበባ እርሻ ድርጅቶች በኦዲቱ ወቅት ላደረጉልን የስራ ትብብር ከልብ እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ-1

## የግብርና ሚንስቴር ስልጣንና ተግባር

- የግብርና እና የደን ልማትን እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የፖሊስ ትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና የሕግ ማዕቀፎችን ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በሰብል ምርት፣ በእንስሳትና ዓሳ እና የተፈጥሮ ሃብት ልማት ግብዓቶች ፍላጎት፣ አቅርቦት፣ ስርጭትና ግብይት ስርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤


- የእፅዋት፣ እንሰሳትና ዓሳ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ በዚሁ ረገድ የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮችን ይመራል ያስተባብራል፣
- የእፅዋትና እንስሳት ጤና አገልግሎትን ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል የሚያስችሉ ሥርዓቶችንና መሠረተ ልማቶችን ይዘረጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ላብራቶሪዎችና ክሊኒኮች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ አቅማቸውን ይገነባል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤
- የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት ምዝገባና ቁጥጥር ይዘርጋል፣ የምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከሀገር በሚወጡት የእፅዋት ቁጥጥር እና እንሰሳትና የእንሰሳት ተዋጽኦዎች ላይ የኳራንቲን ቁጥጥር ሥራን ያስተባብራል፤
- የእንሰሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤ የእንስሳትና የዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምር በመለየት ወደ ገበያ የሚገቡበትን ሥርዓት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ የእንስሳትና የዓሳ ምርትና ተዋጽኦ ምርቶች በሀገር ውስጥ እና በውጪ ገበያ የሚተዋወቁበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፤
- ለገጠር መሬት አስተዳደርና ለተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ዘላቂ የአጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ሀገር አቀፍ መረጃ ያደራጃል፤
- በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በገበያ የሚመራ የእንስሳት ሀብት ልማት፣ ውሃን ማዕከል ያደረገ የሰብልና የእንስሳት መኖ ልማት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የግጦሽ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ልማት አጠቃቀም ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሠራል፤
- ለግብርና የሚውል ውሃን ከዝናብ፣ ከገጸ-ምድር እና ከከርሰ-ምድር ምንጮች በማቀናጀት የውሃ ማቆር ሥራዎች፣ የወንዝ ጠለፋ፣ የምንጭ ማጐልበትና የውሃ መሣቢያ ሞተሮች አጠቃቀም የሚጠናከርበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤ የአርሶ አደሩን እና አርብቶ አደሩን የውሃ አጠቃቀም ክህሎት የበለጠ ለማሳዳግ የድጋፍ እና ማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

- የተፋሰስ፣ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል፤
- የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስዔዎችን ይለያል፣ የመከላከያ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል፤
- የአፈር መሸርሸር መንስዔዎች ልየታ ሥራን፣ የመከላከያ ስልቶች ተነድፈው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ፣ የአፈር ለምነት የሚሻሻልበትን፣ የአፈር ጤንነት የሚጠቅበትን እና ሀገራዊ የአፈር መረጃ ሥርዓትና የአፈር ምርምር ተግባር የሚከናወንበትን ስልት የመንደፍ ሥራን ያስተባብራል፤
- የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ በግብርና ልማት ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመተንበይ የሚያስችል አቅም ይገነባል፣ የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና የመቋቋም አቅምን ለማጠናከር የዕለት ደራሽ ድጋፍ እና የምግብ ዋስትና የሚረጋገጥበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ በገጠር የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፤

- ከመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፣ የሰብልና እንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ በጥናት ግኝት ላይ የተመሠረተ ለቆላማ አካባቢዎች ግብርና ሥራዎች የሚውል የውሃ እና የመሬት አጠቃቀም እና የመስኖ ኤክስቴንሽን ሥርዓት ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
- የግብርና ልማት በገበያ እንዲመራና ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብት የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በገበያ የሚቀርብ ማናቸውንም የሰብል ምርት፣ እንስሳትና ዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

## የግብርና ሚንስቴር መዋቅር

አባሪ 2



**መመዘኛ መስፈርት** አባሪ 3

**ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡- ግብርና ሚኒስቴር**

**የኦዲት አካባቢ፡- የአበባ እርሻ ልማት ምርታማነት አፈፃፀምና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ**

| ተ/ቁ | መመዘኛ መስፈርት | አስተያየት |
|---|---|---|
| 1. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት በአካባቢው እና በመሬት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ እና ዕድገት ለማረጋገጥ የሚረዱ የህግ ማዕቀፎችን ቀርፆ በማፀደቅ ተግባራዊነቱን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ | |
| 2. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ምርቶች ብክነት በአካባቢ እና በኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንዳያስከትሉ የአውትግሮወር እና የኮንሶሊዴሽን የህግ ማዕቀፍ መመሪያ አውጥቶ ሊያስተገብር ይገባል፡፡ | |
| 3. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ለማልማት የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች በተፈጥሮ ሀብት ፡በእፀዋት፡ በእንሰሳት ችግር ማምጣቱን ጥናቶች እና ምርምሮች ሊያካሂድና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| 4. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማቱ የሚጠቀሙት ኬሚካሎች በተገቢው መንገድ ስለመጓጓዛቸው እና በተገቢው መጋዘኖች ውስጥ ስለመከማቸታቸው ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ | |
| 5. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአበባ እርሻ ልማት እድገትና ተደረሻነቱን ለማሻሻል በዘርፉ ለይ የሚጠቀሟቸዉን ግብዓቶች፣ የአበባ ምርቶችና ተረፈ ምርቶች ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የላቦራቶሪ ማዕከል ሊዘረጋና የአበባ አልሚዎችም ስለመዘርጋታቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| 6. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ ልማት ዘርፍ የሚከሰቱት ማነቆዎችን ለመፍታት ጥናቶችን በማካሄድ ጥናቱ ያመጣውን ለውጥ የሚገመግምበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |

| | | |
|---|---|---|
| 7. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ተግባራዊነቱን ሊከታተል | |
| 8. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካባቢ ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት ሁሉን አቀፍ እና የተሳለጠ ለማድረግ መመሪያዎችን ፡ማኖዋሎችን በማዘጋጀት ተግራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 9. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ አምራቾች የሚጠቀሙት የተከለከሉና ጊዜው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የአወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀት ተግባረዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 10. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የውስጥ እና የውጪ የአካባቢ ኦዲት ስለማከናወናቸው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ | |
| 11. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ስራ የሚሰሩ ድርጅቶች በየጊዜው የመሬት ምርመራ እና ማከም ስራ ስለማከናወናቸው ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ | |
| 12. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአበባ እርሻ እና ለሌሎች እርሻ የሚውለው መሬት ልየታ በማካሂድ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| 13. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት በአካባቢው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳደር የስነ ምግባር ደንቡ አፈፃፀም ብቁ እና ቀልጣፋ ለማድረግ ለባለሀብቶች እና ለክልሎች ክህሎት ባላቸው ባለሞያዎች ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ | |
| 14. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማቱ የሚጠቀሙትን ግብዓትመጠንና አጠቃቀም መጠንና አይነት ፣የውሀ፣ የኤሌክትሪክ ፍጆታ አጠቃቀሙን ክትትልና ግምገማ የሚያካሂድበትን ስርዓት ሊዘረጋ እና ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 15. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት የሚሰሩ ድርጅቶች የቴክኖሎጂ እና አመራረት ስልቶች አቅርቦት እንዲስፋፋና አጠቃቀሙም እንዲያድግ በማድረግ፣ ውጤታማነታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ | |
| 16. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ስራን የአፈርና ውሃ አያያዝና | |

| | | |
|---|---|---|
| | አጠቃቀምን፣ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ቀርፆ ተግባራዊነቱን እና ውጤታማነታቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 17. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለዉ የመልካም እርሻ አተገባበር ሥርዓት በሁሉም የአመራረት ሥርዓቶች ተግባራዊ መሆኑን ሊደግፍና ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 18. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች የሚጠቀሙት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ግብዓቶች ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ | |
| 19. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማቱ ሊኖረው የሚችለውን ተፅዕኖ ለመለየትና ለመገምገም የሚረዳ የአካባቢ ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ስለማዘገጀታቸው (ESIA) እና በክልልና በሚመለከታቸው አካላት ስለመገምገሙ ሊከታተል ይገባል። | |
| 20. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች የማህበራዊና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ (Environmental management plan) አዘገጅተው ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 21. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአበባ እርሻ የሚጠቀሙት የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአለም ጤና ድርጅት የተፈቀደና የኬሚካሎቹ መገለጫ እና የአደጋ ማስጠንቀቂያ ምልክቶች አጠቃቀምን በሚገልፅ መልኩ ስለመቀመጡ ሊከታተል ይገባል፡፡ | |
| 22. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች አካባቢ ከመጠበቅ አንፃር የተቀናጀ ተባይ መከላከል /IPM/ እንዲተገበር ሊደግፍና ሊከታተል ይገባል፡ | |
| 23. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅት ሀገራዊና እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች፣ የስራ አካባቢ ምቹትን ከስራ ጋር ተዛማች የሆኑ ስልጠናዎች፤ የደህንነት መጠበቂያ ቁሶች ፤የጤና ምርመራ ድንጋጌዎች መሰረት የሰራተኛን የሰብአዊ መብት መከበሩን ስርዓት | |

| | | |
|---|---|---|
| | ዘርግቶ ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ | |
| 24. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ እርሻ ድርጅቶች የሚሰሩ ሴት ሠራተኞች ጤንነታቸውና እና የስራ ቦታ ደህንነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸው ተጠብቆ እየሰሩ ስለመሆናቸው ከሚመለከተቸው አካላት ጋር በመሆን ድጋፍ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| 25. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአበባ እርሻ ድርጅቶቹ የሚወጡ ቆሻሻዎች በሚከማችበት፣ በሚጓጓዝበት፣ በሚወገድበት፣ ሰርዓት መዘርጋቱንና በሰዎችና በእንስሳት ጤና እና በአካባቢ ብክለት በመያስከትል መልኩ ቆሻሻ በአግባቡ መያዝና መወገዱን ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ | |
| 26. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ድርጅቶች በአካባቢ ላይ ስለሚያደርሱት ተፅእኖ ለአካባቢ ጥበቃ የሚሆን ክፍያ እንዲከፍሉ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ሊከታልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ | |
| 27. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአበባ እርሻ ልማት የሚያስፈልጉት መሠረት ልማቶች፡ ሎጀስቲክ አገልግሎት ሊያመቻችና አቅርቦቱ ለታለመለት ዓላማ መዋላቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል ፡፡ | |
| 28. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ እርሻ ልማት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች የማህበራዊና የአካባቢያዊ ኃላፊነት ደረጃዎችን አሟልተው እየሰሩ ስለመሆናቸው ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ጋር በመተባበር ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል። | |
| 29. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በአበባ እርሻ ልማት ዙሪያ ጠንካራ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ለአልሚዎች የተላለፈውን መሬት ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ የመሬት ብክነትን ሊያስወግድ ይገባል። | |
| 30. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ እርሻ ልማት ግብይት ወቅታዊ፣ ሀገራዊና አለም አቀፋዊ የምርትና የግብይት እንዲሁም ተያያዥ መረጃዎችን ሊሰበስብ፣ ሊያደራጅ፣ ሊተነትንና በወቅቱም ለተጠቃሚዎች ተደራሽ | |

| | | |
|---|---|---|
| | ሊያደርግና ተፈጻሚነቱን ሊከታተል ይገባል። | |
| 31. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአበባ እርሻ ልማት ስራዎችን ዕድገት ፍጥነትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ ተሞክሮዎችን በመቅሰም፤ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበትን ቋሚ የምክክር መድረክ በማመቻቸት የልምድ ተሞክሮችን በመቀመር ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ | |
| 32. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን የአበባ እርሻ ምርቶች ሳይበላሹ እንዲሰበሰቡ፣ እንዲከማቹ፣ እንዲጓጓዙ እና ለገበያ እንዲቀርቡ የሚያስችል የቅዝቃዜ ሰንሰለትን የሚያስጠብቅ የሎጂስቲክስ አገልግሎትን የሚያበረታታ ሥርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል:: | |
| 33. | ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአበባ አልሚ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ሲያወጡ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን እንዲሁም ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቷ እንዲሰራ ሊከታተል ይገባል፡፡ | |

# አባሪ 4

## ለአበባ እርሻ የተሰጣቸው መሬት ያላለሙ ድርጅቶች

- ✓ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ኢንቨስትመንት  በወሊሶ 376 ሄክታር፤ ሆለታ 117 ሄክታር ተሰጥቶቻቸው ስራ ጀምረዉ በ2009/2010  ስራውን ያቆሙ ሲሆን፡- እስካሁን ወደ መንግስት መሬት ባንክ እና ወደ ሌላ የልማት ስራ ያልገባ መሆኑ፣
- ✓ አልሚ ድርጅቶቹ ማለትም፤ ጉና ትሬዲንግ(ሰበታ) እና መሀመድ ኢብራሂም(በቢሾፍቱ) የአበባ እርሻ ድርጅቶች እያንዳንዳቸው በቅደም ተከተል 20 ሄክታር እና 10.5 ሄክታር በጠቅላላው ሰላሳ ነጥብ አምስት (30.5) ሄክታር እንዲያለሙ ተሰጥቷቸው ያላለሙና ስራውን ያቋረጡ ሲሆን ወደ መንግስት መሬት ባንክ ያልገባ መሆኑ፤ አሰላ ፍለወር 20 ሄክታር  እንዲያለሙ የተሰጣቸውና  2.5 ሄክታር ተጨማሪ ከገበሬ በሊዝ የገዙ ሲሆን 2.5 ሄክታር ገና ያላለሙት መሆኑ፤ ሳሮን ሮዝ 20  ሄክታር 16 ሄክታር ልማት ላይ ሲውል 4 ሄክታር ገና ያላለማ መሆኑ፤
- ✓ እንዲሁም ዲፕሪም ቢዝነስ 86 ሄክታር የተሰጣቸው ሲሆን፤ 7 ሄክታር አበባ እንደሚያመርቱበት የተሰጣቸው ቢሆንም 79 ሄክታር ያለማ መሆኑ፡ ቲናው ቢዝነስ በ47 ሄክታር የተሰጣቸው ሲሆን ስራ ላይ ያለውት 32 ሄክታር ሲሆን  15ሄክታር ገና ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣ ለአብሲኒያ ፍላወር ሃ/የ/የግ/ማ እንዲያለማ የተሰጠው መሬት 34 ሄክታር ሲሆን 11.7 ሄክታር  ብቻ ላይ እለሙ ሲሆን በ22.3 ሄክታር ገና ያላለማው መሬት መኖሩ፤ ድሬ ባይ ኮላር የአበባ እርሻ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በእርሻዉ በባለቤትነት ከተያዘዉ 21 ሄክታር መሬት ዉስጥ ጥቅም  ላይ የዋለው 1/5 ኛዉ ወይም 4.5 ሄክታር ብቻ ሲሆን ከተረከቡት መሬት 16.5 ሄክታር ገና ያላለሙት በመሆኑ አሁን ካለዉ የመሬት ጥበት አኳያ ሲታይ ከፍተኛ ብክነት መሆኑ፣

ከላይ የተገለፀው ሀሳብ በሰንጠዥ መልክ ሲገለፅ፡

| ተ.ቁ | የአበባ እርሻ ድርጅት ስም | የአበባ ልማት እንዲለማበት የተሰጠው መሬት /በሄክታር/ | ልማት ላይ መዋል እያለበት ያልለማ መሬት/ በሄክታር/ |
|---|---|---|---|
| 1 | ጉና ትሬዲንግ (ሰበታ) | 20 | 20 |
| 2 | መሀመድ ኢብራሂም(በቢሾፍቱ) | 10.5 | 10.5 |
| 3 | አሰላ ፍለወር | 22.5 | 2.5 |
| 4 | ሳሮን ሮዝ | 20 | 4 |
| 5 | ዲፕሪም ቢዝነስ | 86 | 79 |
| 6 | ቲናው ቢዝነስ | 47 | 15 |
| 7 | አብሲኒያ ፍላወር | 34 | 22.3 |
| 8 | ድሬ ባይ ኮላር | 21 | 16.8 |
| 9 | በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ኢንቨስትመንት በወሊሶ 376 ሄክታር | - | 376 |
| 10 | በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ኢንቨስትመንት ሆለታ 117 ሄክታር | - | 117 |
| 11 | ጠቅላላ ያልለማ መሬት ድምር | | **662.8** |